# ምዕራፍ ፳፱

# ኮምኒዝም ወደቀ

## አስራ ስድስት ዓመት ወይስ ቀጣዩ መስከረም ሁለት?

ጊዜው የጸሓዩ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ወድቆ ወታደሮች አገሪቱን እየተቆጣጠሩ የነበረበት ነው። አገራቸውን የሚወዱት ወንጌላዊ ኬዳም ለጸሎትም ሆነ ለእውቀት እንዲሆናቸው ስለአገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች የሚተላለፈውን ዜና በአንክሮ ይከታተላሉ። እናም የንጉሡን መውረድ፣ የመሬት ላራሹን መታወጅ፣ የብዙ ንጹኃን ዜጎችን የሞት ፍርድ ሳይቀር በሬድዮ እያደመጡ ጉዳዩን በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባሉ። በነገሩ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሃሳብ ምን እንደሆነም ይመረምራሉ። ሁል ጊዜ አዲስ የተቋቋመው የደርግ መንግስት የሚያወጣውን ተከታታይ መግለጫ ከመከታተል ባሻገር እድሉን ሲያገኙ ከውጪ በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉትን እንደ 'የጀርመን ድምጽ ራዲዮ' ያሉትን ሳይቀር ያዳምጣሉ።

አንድ ቀን ግን በአገሪቱ ታላቅ ፋይዳ ያለው ጉዳይ ሲወሰን ያኔ እንደ ብርቅ እና የኃብታም ንብረት ይቆጠር በነበረው ባለ ነጭ እና ጥቁር ቴሌቪዥን የመመልከት ዕድል ገጠማቸው።

በወቅቱ አቶ ታምራት እሳቴ የሚባሉት ወዳጃቸው ባለቤታቸው አርፈው ስለነበር ወንጌላዊ ኬዳም እና አቶ ደምሴ ማዴ ለቅሶው ትኩስ የነበረባቸው ቀናት ካለፉ በኋላ ለማስተዛዘን እና አብረው ለመጸለይ ወደ አቶ ታምራት ቤት ሄደዋል። በዚያች ኬዳም እና አቶ ደምሴ በተገኙባት ምሽትም አቶ ታምራት ቤት ቴሌቪዥን ስለነበር በቴሌቪዥን አገሪቱን እያስተዳደረ የነበረው የደርጉ ሊቀ መንበር ጓድ መንግስቱ ኃይለ ማርያም የአገሪቱ ርእሰ ብሔር መሆናቸው ተገለጸ።

ወንጌላዊ ኬዳም እና አቶ ደምሴም አቅደው በመጡ መሠረት ያንን ዓርብ ማታ ከአቶ ታምራት ጋር ሆነው ሲጸልዩ አደሩ። በዚህ ሌሊት ጸሎታቸው ላይም በምሽቱ ከተላለፈው ዜና ጋር በተያያዘ እግዚአብሔር የሚከላከለው ክፉ እና የሚሠራው መልካም ነገር እንዲኖር ጸለዩ። በዚሁ የጸሎት ሰዓትም እግዚአብሔር መንግስቱ ለ16 ዓመታት በስልጣን ላይ እንደሚቆይ ተናገራቸው። በማግስቱ ቅዳሜ ጠዋትም

*ወንጌላዊው ስለ መንግስቱ የሥልጣን ቆይታ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ለነ አቶ ታምራት ተናገሩ።*

*ይህ ዜና ከተሰማ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሀገር ወዳዱ እና ቆራጡ መሪ መንግስቱ ኃይለ ማርያምም ከአጋሮቻቸው ጋር በመሆን እግዚአብሔር መኖሩን የሚክደውን የኮምኒስት ርዕዮተ ዓለም ይበጀናል ብለው መረጡ። እግዚአብሔር መኖሩን የሚያምኑትንም ያሳድዱ እና እምነታቸውን ለማስጣል ይታገሉ ጀመር።*

*በዚህም ብቻ ሳያበቃ ወታደራዊው መንግስት የሚገዳደሩትን ሁሉ እየጠራረገ ያስወግድና በመዣረያ ይደመስስ ገባ። መስከረም ሁለት ንጉሣዊው አገዛዝ የተገረሰሰባት ዕለት ስለነበረችም የአብዮቱ ድል አድራጊነት መታሰቢያ ተደርጋ በአገሪቱ የታላቅ በዓል ማክበሪያ ቀን ሆነች።*

*የዚሁ በዓል መከበሪያ ቀን እየተቃረበ ባለበት አንድ ዕለትም ታደሰ የሚባል ወንጌላዊ ወደ ወንጌላዊ ኬዳሞ ቢሮ በመምጣት መስከረም ሁለት የአብዮት በዓል በሚከበርበት ቀን ወታደራዊው መንግስት እንደሚወድቅ እግዚአብሔር እንደተናገረው ነገራቸው። ኬዳሞም "ይህንን ነገር ተው ለሌላ ሰው አትናገር። እኔ ለ16 ዓመታት እንደሚቆይ እግዚአብሔር ገና መንግስቱ ኃ/ማርያም በተሾመበት ዓመት ተናግሮኛል።" አሉት። ወንጌላዊ ታደሰም በእርሳቸው ሃሳብ ሊስማማ አልወደደም። በመጨረሻም "ይህንን ነገር ከዚህ ወጥተህ ለማንም እንዳትናገር፤ ከተሰማብህ ትታሰራለህ አሊያም ልትገደል ሁሉ ትችላለህ።" ብለውሸኙት።*

*እርሱ ግን ከእግዚአብሔር የተቀበለው መልእክት ስለመሰለው በድፍረት በአንድ የጸሎት ጉባኤ በሚካሄድበት ስፍራ ከጌታ ተቀበልኩት ያለውን መልእክት ተናገረ። ክፉ አጋጣሚ ሆኖም በተናገረበት ስፍራ ካድሬዎች ተመሳስለው ገብተው ስለነበረም ተይዞ ማዕከላዊ ተወስዶ የአምስት ዓመት እስራት ተፈርዶበት ከብዙ መሳቀቅና እንግልት በኋላ እግዚአብሔር ነፍሱን አትርፎለት ተለቀቀ።*

*ወንጌላዊ ታደሰ ከእስር እንደተፈታም በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ወደ ጌጃ ቃለ ሕይወት በመሄድ ወንጌላዊ ኬዳሞን ፈልጎ "በአንተ ላይ ያለው የእውነት መንፈስ ነው።" ብሎ መናገር ነበር። ይህ ወንድም በመጨረሻ በገጠመው ነገር ሳይሰናከል ከዚያም በኋላ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ጌታን እያገለገለ መኖሩን ቀጥሏል።*

*ኬዳሞ እንደተናገሩትም መንግስቱ ኃይለ ማርያም ከአገር ኮብልሎ እስከ ሸሸበት ጊዜ ድረስ ለ17 ዓመታት ያህል በሥልጣን ላይ ቆየ። የተጠቀሱት 16 ዓመታትም በ1983 ዓ.ም ተጠናቅቀው ከስልጣን የሚሰናበትበት ጊዜ ይፋጠን ጀመር።*

---------------------------//---------------------------

# እግዚአብሔር ለዘለዓለም ንጉሥ ነው

የደርግ መንግሥት አገሪቱን በሚገዛበት ዘመን የነበረብንን መከራ ሁሉ አልፈን የምናርፍበት ዘመን መጣ፡፡ የደርግ ዘመን ማብቂያ ላይ እኔ አሜሪካ ሄጄ ወደ አዲስ አበባ የተመለስኩት በመጋቢት ወር ነበር፡፡ እግዚአብሔር እንደተናገረኝም የደርግ መንግስት የሥልጣን ዘመን መንግስቱ ኃ/ማርያም መሪ በሆነ ልክ በ16ኛው ዓመት ላይ ተጠናቀቀ፡፡

እኛም በጊዜው በሰሜን ይካሄድ የነበረው ጦርነት ከምን እንደደረሰ በየጊዜው ያለውን ለውጥ በሬድዮ እንከታተል ነበር፡፡ በተለይ እኔ ዘወትር ለጸሎት እንዲሆነኝ ሬድዮ መስማት እና ቴሌቪዥን ማየት እፈልግ ነበር፡፡ እዚህ ጋ ይህ ሬድዮ የማዳመጥ ልምዴ በጣም እንደሚጠቅም ያየሁበትን አንድ አጋጣሚ ለማንሳት እወዳለሁ፡፡

ያኔ የደርግ መንግስት ሥልጣን እንደያዘ የተለያዩ አዋጆች፣ መግለጫዎች እና ሹም ሽሮች በተከታታይ በሬድዮ ይተላለፉ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ አንድ በጣም ኃይለኛ አብዮተኛ የሆነን ግለሰብ የአዲስ አበባ ከተማን የሚያስተዳድረው የፖለቲካ ቢሮ ሊቀ መንበር አድርገው ሾሙት፡፡ ሰውየውም ገና እንደተሾመ በሬድዮ የእኛን እምነት ለመግለጽ በዚያ ዘመን አጠራር እንደሚሉት "ርካሽ ባህልን በሙሉ ከአዲስ አበባ እናስወግዳለን፡፡" ብሎ ተናገረ፡፡ በዚህ ጊዜ እኛም የእርሱን ንግግር ከሰማን በኋላ በኃይል ያለመታከት ወደ እግዚአብሔር መጮህ እና መጸለይ ጀመርን፡፡ እግዚአብሔርም ሰማን፡፡ ሰውዬውም ወዲያውኑ ብዙ ሳይቆይ ታመመ እና እግሩ ሳይቀር ሽባ ሆኖ ሥራውን ሲያቆም ባለቤቱም ጌታን አገኘች፡፡

ያ ሰው ታዋቂ ባለ ሥልጣን እና የተፈራ የኢ.ሠ.ፓ ካድሬ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን እኛ መረጃውን ሰምተን የጸለይነውን ጸሎት መልሶ ሰውየው በሬድዮ እና ቴሌቪዥን የተናገረውን ሳይፈጽም አስቆመው፡፡

በደርግ መንግስት የአገዛዝ ዘመን የነበሩትን አስፈሪ ወቅቶች እግዚአብሔር በድል እያሻገረን ሞት በረከሰባቸው ጊዜያት "አንድ ቀን ሞቼ እኔ በምሞትበት ቦታ ወንጌል ይዘራበታል" እያልኩኝ፣ እኔንም ሆነ አብረውኝ ጌጃ ያገለገሉ ወገኖች እግዚአብሔር እንደሰጠን የተስፋ ቃል እንደ ዓይኑ ብሌን ጠብቆን ተሻገርን፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም ከመዘጋት ስጋት ወጥታ በሰላሙ ዘመን እነበሯት አባላት በብዙ እጥፍ በዝታ ጭራሽ በስደቱ ዘመን ሺዎች የሚገለገሉባት ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ማዕከል ሆነች፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስጋቱ በጣም ባየለበት ወቅት ለእኔ እና ለሽመልስ ወዳጆ የኑሮ ሁኔታ በመጨነቅ ሠርተን ገቢ ማግኘት የምንችልበትን መኪና ወይም የንግድ ድርጅት ሊያቋቁሙ ሲያስቡ የነበረው ቀርቶ እኔ እዚያው ጌጃ ወንጌልን እየሰበክሁ የተነገሩኝ 16 ዓመታት ተፈጸሙ፡፡

በእኔ እይታ ያንን ዘመን ሳስበው ደርግ ፈጽሞ የሚወድቅ አይመስልም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ስላደረገው ግንቦት ሃያ ዕለት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አዲስ አበባ ገባ። ይህ እውን ከሆነ በኋላም ክርስቲያኖች ሁላችን እግዚአብሔርን አመሰገንን። የእምነት ነጻነትም ስለተሰጠን ወዲያውኑ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ታላቅ ኮንፍረንስ በአዲስ አበባ ስታዲየም ተዘጋጀ። በዚሁ በአገራችን የወንጌል ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አደባባይ የወጣንበትና ትልቅ ስፍራ በሚይዘው ታሪካዊ ኮንፈረንስ ላይም እኔ እንድሰብክ ተመረጥሁ።

እናም ኮንፍራንስ ላይ እንድሰብክ በጊዜው የኅብረቱ ዋና ጸሐፊ የነበረው አቶ ሙላቱ ታዬ "እግዚአብሔር ለዘለዓለም ንጉሥ ነው" የሚል ጥቅስ ከመዝሙረ ዳዊት ሰጠኝ። እኔም በዚህ ርእስ ላይ እግዚአብሔር ለዘለዓለም ንጉሥ እንደሆነና ትላንት ንጉሥ እንደነበረ፤ አሁንም ንጉሥ እንደሆነ ወደፊትም ንጉሥ ሆኖ እንደሚቀጥል ሰበክሁ። እናም "ስድስት መቶ ሺህ ወታደር፤ ብዙ ታንክ እና ከባድ መሣሪያ የነበረውን የደርግ ጦር የጣሉት ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.ዎች የኩበት እረኞች ነበሩ። ነገር ግን እግዚአብሔር እነርሱ ድንቅ ተዓምራት ሠርቶ የማይገረሰሰው ተገረሰሰ።" እያልኩ ሰበክሁ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ የኛ ሰዎች ከዚህ ስብከት የተነሳ ልታሰር እንደምችል ይነግሩኝ ነበር። እኔም "ያለውን እውነት ነው የተናገርኩት፤ ምንም የሚያስፈራኝ ነገር የለም፤ እኔ አልፈራም" አልኳቸው። ሰዎቹም ከዛሬ ነገ ይታሠራል እያሉ እየጠበቁ ምንም ነገር ሳይገጥመኝ አለፈ።

ከዚህ በኋላም በየቦታው የተዘጉ ቤተ ክርስቲያናት ይከፈቱ ጀመር። ከኛ ጋር ቤተ ክርስቲያናቸው ሲዘጋ እያለቀስን አብረን የጸለይንላቸው እና በኋላም ክፉውን ጊዜ አብረውን ያሳለፉ የሰፈረ ገነት ቤተ ክርስቲያን ስትከፈት ታላቅ የምስጋና ፕሮግራም ነበረ። እናም ባዘጋጁት የምስጋና ፕሮግራም ላይ እኔ እንድሰብክ ነበር የጋበዙኝ። የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ስትከፈትም እንዲሁ በተካሄደው የምስጋና ፕሮግራም ላይ ተጋብዤ ሄጄ አገልግያለሁ።

ኮምኒዝም ተረት ሆኖ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን እና ለሕዝቡ ነጻነትን ሲሰጥ የማይቻልና የማይሆን ይመስል ስለነበር በጣም አስደናቂ ተዓምራት ነበር የሆነው። እኔም ይህንን በዓይኔ ስላየሁ የእግዚአብሔር ታላቅነት፣ ንጉሥነት እና ጌትነት ምስክር ስለሆንኩ ከዚያ ጊዜ በኋላ አገልግሎቴ እና ሕይወቴ ሁሉ እንደገና ታደሰ። ያን ጊዜ ያዘጋጀኋቸው ስብከቶች ሁሉ የሚያስደንቁና ሰዎች ሁሉ የሚባረኩባቸው ነበሩ። እኔም ይህንን ድንቅ አገልግሎት በኢትዮጵያ ምድር የሚያዳርሱ ተተኪዎችን ስለማዘጋጀት አስብ ጀመር።

ይህ ታላቅ ዕድል ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጠ በኋላም በየቦታው እንቅስቃሴው በመስፋፋቱ አዳዲስ ነገሮችም ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር። በዚሁ ጊዜ የእምነት ነጻነት ከመጣ በኋላ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል እኔ ባለሁበት የተፈጠረን አንድ አጋጣሚ አንስቼ ለማውሳት እሻለሁ።

የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት አገሪቱን መምራት ከጀመረ በኋላ የእምነትም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም መብት ተረጋገጠ። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አገሪቱን ማስተዳደር ጀምሮ ጥቂት ጊዜያት ካሳለፍን በኋላም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ታላቅ ዓመታዊ የመሪዎች ኮንፍረንስ ከመላ አገሪቱ ለተውጣጡ ሁለት ሺህ ያህል መሪ አገልጋዮች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 6 ኪሎ ካምፓስ አዘጋጀ። በኮንፍረንሱ ላይ እንዲያገለግሉም ከምዕራብ አፍሪካ ዶ/ር ቶኮምቦ አዲያሞ የሚባሉ እንግዳ ተጋብዘው ነበር። እኔም ከእኚሁ እንግዳ ጋር አብሬ ኮንፍረንሱ ላይ እንዳገለግል ዕድል ተሰጥቶኝ አገለገልኩ።

በዚሁ ለሳምንት ያህል በቆየ ታላቅ ጉባኤ ላይም ዶ/ር ቶኮምቦ በኢትዮጵያ አሁን ነጻነት በመሰጠቱ ወንጌላውያን አማኞች በአገር ደረጃ አወንታዊ ተጽእኖ የሚያመጣ እና አገሪቱን መምራት የሚችል የክርስቲያን ፓርቲ ማቋቋም እንዳለብን መልዕክት አስተላለፉ።

ይህን በሰማሁኝ ጊዜ እኔም ነገሩ አስፈላጊ እንዳልሆነ ስለማምን የክርስቲያን ፓርቲ እንደማያስፈልገን ጽኑ አቋም ይዤ ተናገርኩ። ይህንን ሃሳቤን ሳጠናክርም ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ካልመጣ በስተቀር አንድ ቀን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለቤተ ክርስቲያን አሳልፎ ይሰጣል። በተለያየ ዘርፍ ያለው መሪነት እና ሥልጣን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ይሆናል። ነገር ግን አሁን እኛ የክርስቲያን ፓርቲ ካቋቋምን የሌላ ተፎካካሪ ፓርቲን ድካም እና ስለ እነርሱ ክፉነት ነው የምናወራው። በፓርቲ ስለምንለያይም ለሰዎች ወንጌል መስበክ አንችልም። እርስ በርስ መፎካከር እና አንዱ ስለ ሌላው በውሸትም ይሁን በእውነት ስም የመጠፋፋት ዘመቻ ነው የምናካሂደው።

በዚህ ዓይነት በሌሎች አገራት የተቋቋሙ ፓርቲዎች አሉ። ነገር ግን ፓርቲዎቹ ስም ብቻ ነው የያዙት እንጂ ወንጌልን ጥለዋል። ከሌሎች ወገኖች ጋርም ጠላቶች ሆነዋል። እዚህም የሚመጣው ያው ስለሆነ ፈጽሞ አያስፈልገንም። ነገር ግን ክርስቲያን ሆኖ በግል ወደ ፓለቲካ መግባት እና ለመሪነት መወዳደር የፈለገ ግን መግባት ይችላል። ያን ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች እንዲመረጡ ልንደግፍ እንችላለን።" አልኩ።

ዶ/ር ቶኮምቦ እኔ ሃሳቡን በመቃወም ያቀረብኩትን ስብከት ከሰማ በኋላ፤ አብረን ለውይይት ቁጭ ብለን ተነጋገርን። በመጨረሻም እርሱም በኔ ሃሳብ ተስማማ እና ፓርቲ የማቋቋሙ ሃሳብ እዚያው ተዳፍኖ ቀረ።

እኔ በዚያ ኮንፍረንስ ላይ እንደተናገርኩትም አሁን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አሳልፎ ለቤተ ክርስቲያን እየሰጠ ነው። በደቡብ ክልል፣ በወላይታ፣ በሃዲያ፣ በጌዴኦ፣ በከንባታ በብዙ የመሪነት ቦታዎች ላይ የተቀመጡ ክርስቲያኖች ናቸው። አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመሩም ሰዎች አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያን ያደጉ ናቸው። እግዚአብሔር ገና በብዙ ቦታዎች ላይ ያለ ምንም አድልዎ የሚያስተዳድሩና በጽድቅ የሚፈርዱ ታማኝ አገልጋዮችን እና እውነተኛ ክርስቲያኖችን ያስቀምጣል። ከዚያ ከጨለማ ዘመን አሳልፎ

ለዚህ ድል ያበቃን አምላካችን እግዚአብሔር በቃሉ እንደተናገረውም እርሱ ለዘለዓለም ንጉሥ ነው።

ያገኘነው የእምነት ነጻነትም በየሰዉ ቤት ተደብቆ የሚያመልከው ሁሉ ወደ አደባባይ እየወጣ ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት እንድታድግ ጥርጊያ መንገድ ከፍቶልናል። ይሁንና እኔ በዚያ ክፉ ዘመን የነበረንን ትጋት ከዛሬው ጋር ሳስተያይ አሁንም የዚያ ዘመን ትጋታችንን እናፍቃለሁ። ያኔ የጌጃ ጸሎት ቤታችን ከሌሊቱ 11:00 ሰዓት በሰው ይሞላ የነበረ ሲሆን ዛሬ በ4:00 ሰዓት እንኳን ሰዉ ተዝናንቶ፣ አርፍዶ ነው የሚመጣው። ያኔ ለአማኞች እግዚአብሔር እና የወንጌል መልእክት ብርቅ ነበረ፣ ዛሬ ግን ሰዉ እግዚአብሔር ራሱ ስለቀለለበት አሜን የሚለው እንኳን እግዚአብሔር ተናግሮት ሳይሆን ዘማሪ እና ሰባኪ ጎትጉቶት ነው። እርሱንም የሚያደርገው በውሸት እና በማይፈጸም የግል ጥቅም ተስፋ ተደልሎ ነው። ይህንን ሳይ ልቤ ቢያዝንም እግዚአብሔር ያንን አስፈሪ የማይወድቅ የሚመስል ኃያል መንግስት ገርስሶ የእምነት ነጻነትን ሰጥቶ ወደ አደባባይ እንዳወጣን በማሰብ ተጽናንቼ ጌታን አመሰግናለሁ። በእውነትም እግዚአብሔር ለዘለአለም ንጉስ ነው።

# ምዕራፍ ፴

# የአውሮፓ የአገልግሎት ቆይታ

## የበረታ ህመም እና የጌጃ ምዕመናን ምልጃ

*የኬዳሞ የጌጃ የቆይታ ዓመታት ሁለት አስርት ዓመታትን ደፈኑ። ወንጌላዊውም አንገታቸውን ያስገቡበት ቀንበር እስከ መጨረሻው የማይጥሉት ሆኖ እንጂ የሙያ ሥራ ቢሆን ግን የጡረታ መውጫ እድሜአቸው ተቃርቧል።*

*ይሁንና ወንጌላዊው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ፍቅር ለሌሎች ለመናገር ትጉህ ናቸው። እግዚአብሔርም ከጌጃ አልፈው ነፍስ ሊዘሩበት የሚገባውን የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ሞት ተናግሯቸው የራሱን የማሰማሪያ ጊዜ እየተጠባበቀ ነው።*

*በድንገት ግን ወንጌላዊው በ1986 ዓ.ም በምን እንደመጣ ያልታወቀ በሽታ ይዟቸው አልጋ ላይ ዋሉ። መንስኤው ያልታወቀው ይህ ሕመም ጠንቶባቸውም እጅ እግራቸው እና መላ ሰውነታቸው ይንቀጠቀጥ ገባ።*

*ይኸው ወንጌላዊውን ክፉኛ ይዞ የሚያሰቃያቸው ህመም በድንገት ከሆዳቸው ይነሳ እና መላ ሰውነታቸውን ያዳርሰዋል። ችግሩን ለማወቅም በየሆስፒታሉ ይዞሩ ጀመር። ፍል ውሃ ሆስፒታል፣ የአቶ ተስፋጺዮን ባለቤት ያሉበት ጳውሎስ ሆስፒታል፣ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑት እነ ሲ/ር እቴነሽ ያሉበት ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ወዘተ... እየተዟዟሩ ልዩ ልዩ ምርመራ እየተደረገላቸው ቢታዩም ማንም የበሽታውን ምንነት ሊያውቅ አልቻለም።*

*አንዳንዶቹም ራጅ አንስተውና ደም መርምረው ህመሙን ማወቅ ሲሳናቸው ሊሠራ ይችላል ያሉትን መድኃኒት በመስጠት በሽታውን ለማስቆም እና ሕይወታቸውን ለማዳን ሞከሩ። ነገር ግን በጤናቸው ላይ ምንም መሻሻል ባለመታየቱ ለሁለት ወራት ያህል አልጋ ላይ ቆይተው በመጨረሻ ቤተሰብ ተስፋ ወደ መቁረጥ እርሳቸውም ወደ መዳከም ይሄዱ ጀመር።*

*በዚሁ ፍጹም ተስፋ በተቆረጠበት ጊዜ ላይም አንድ ቅዳሜ ቀን የጌጃ ቃለ ሕይወት ሽማግሌዎች እና ወንጌላውያን ወንጌላዊውን ሊያዩ እና ሊጸልዩላቸው ወደ ቤታቸው መጡ። ሁኔታቸውን አይተው ጸልየው ሲወጡም ሊሞቱ እንደሚችሉ ያሰቡት ወንጌላዊ ኬዳሞ አንድ ነገር ተናገሩ። "በቤተ ክርስቲያናችን ያለው ጉባኤ የእኔን መታመም ሰምቶ ሳይጸልይልኝ ሞቴን ሰምቶ እንዳያዝን እባካችሁ ቶሎ በጠና መታመሜን ለሕዝቡ ንገሩልኝ።" አሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች እና አገልጋዮችም የኬዳሞን አደራ ተቀብለው ሄዱ።*

*ኬዳሞ ይነገርልኝ ባሉት መሠረትም ጌጃን ለሁለት አስርት ዓመታት በጽናት አገልግለው ለብዙዎች መዳን፣ ለብዙዎች መታነጽ፣ ለብዙዎችም የጌታ አገልጋይ መሆን ምክንያት የሆኑት የወንጌል አርበኛ በጽኑ የመታመማቸው ዜና በቤተ ክርስቲያኒቱ ባለው የሦስት ፈረቃ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ ታወጀ። የጌጃ የሦስት ፈረቃ ፕሮግራም ታዳሚ ጉባኤም ፈጣን ምላሽ ሰጠ። ምዕመኑ አገልጋዩ በጠና መታመማቸውን እና ተስፋ መቆረጡን ሲሰማ ተስፋ ወደሚሰጠው ጌታ ለመጮኽ ወሰነ። ስለሆነም የመጀመሪያውን ፈረቃ የተካፈሉ ሁሉ የሰዓቱ ፕሮግራም አልቆ ከአዳራሽ ሲወጡ በቀጥታ ወደ ጸሎት ክፍል አመሩ። የሁለተኛው ፈረቃ እስኪያልቅም በጸሎት ወንጌላዊውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሲሰጡ የእግዚአብሔር ክንድ ተገልጦ እንዲዳስሳቸውም ሲማልዱ አረፈዱ። በሁለተኛውና በሦስተኛው ፈረቃም እንዲሁ ተደረገ። እግዚአብሔርም የታላቁን ጉባኤ ጸሎት ሰምቶ ፈጣን ምላሽ ሰጠ።*

--------------------//------------------

## ከአሊጋ ወደ አውሮፓ

ሕመሜ ጸንቶ በጣም ተስፋ ተቆርጦ ስለነበር ቤተሰቤ ራሱ ሁኔታዬ እየከፋ ሲሄድ የእኔን የለቅሶ ሥነ ሥርዓት በጥሩ ሁኔታ ለማካሄድ ዝግጅት ሁሉ ጀምረው ነበር። ለለቅሶ ይረዳ ዘንድ ፎቶግራፌ ተባዝቶ ተዘጋጀ፤ ለሰዎች ሁሉ ሁኔታው ተነገረ።

እንድተርፍ ለማድረግም በአዲስ አበባ ያሉትን የመንግስት ሆስፒታሎች አዳርሼ አንዳንድ የጤና ባለ ሙያዎች እየጠቆሙም እንደ ኦልድ ኤይር ፖርት ክሊኒክ ባሉ ታዋቂ ሐኪም ባላቸው ክሊኒኮች የተለያየ ምርመራ ተደርጎልኝ ኢንዶስኮፒ የመሳሰለውን ሁሉ ታየሁ። ግን ምንም ተስፋ አልተገኘም። ስለዚህም እኔን ጨምሮ ሁሉም ሰው ተስፋ ወደ መቁረጡ ሄደ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን ነው እንግዲህ የጌጃ ሽማግሌዎች እና ወንጌላውያን ሊጠይቁኝ የመጡትና እኔም "ጉባኤው ሳይጸልይልኝ እንዳልሞት።" ያልኳቸው። ከዚያም እነርሱ እኔጋ በመጡ በማግስቱ እሁድ ቤተሰቤ ለአየር ለውጥ ሳሉን አስተኝተውኝ በተኛሁበት ሆኜ የእግዚአብሔርን ክንድ እጠባበቅ ነበር።

ተጋድሜ ሕመሜን እያዳመጥኩ እያለም በድንገት ውስጤ ልክ በቢላዋ እንደመቆረጥ ያህል ጽኑ ሕመም ይሰማኝ ጀመር። "በፊት እንደ ፈንጂ የሚፈነዳ ዓይነት ሕመም ይሰማኝ ነበር፤ አሁን ደግሞ እንደ ቢላዋ ይቆርጠኝ ጀመር።" አልኩኝ ለራሴ። ነገር ግን ወዲያው "ዛሬ የአንተን በሽታ ቀዶ ጥገና (ኦፐራሲዮን) የሚያደርግ ነው የመጣው።" አለኝ አንድ ድምፅ። ልክ ይህን ድምፅ እንደሰማሁም ወዲያውኑ ራዕይ መመልከት ጀመርኩ።

በራዕዩ ውስጥም ከአንድ ፈረንጅ ጋር ለምለም ሣር ያለበት ሰፊ መስክ ላይ እያቋረጥን እንሄዳለን። ብዙ ከሄድን በኋላም ወደ አንድ ሰማያዊ ቀለም የተቀባ አጥር ያለው ግቢ ጋ ደረስን። እንደደረስንም ፈረንጁ ወደ ግቢው መግቢያ በር ተጠግቶ ጫን የሚደረግ የመክፈቻ መዝጊያ ቁልፉን ሲነካው በሩ ተከፈተ። ከዚያም ነጭ ወንበር ከግቢው ወደ ውጪ ወጣና ፈረንጁ በዚያ ምቹ እቅፍ አድርጎ የሚይዝ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ ወንበሩ ወደ ውስጥ ገባ። እኔም "ሰውየው ገብቶ እኔ ልቀር ነው እንዴ?" እያልኩ እያሰብኩ ሳለ ሌላ ወንበር ወጣ እና እኔም ተቀምጬበት ገባሁ።

ግቢው ውስጥ ከገባን በኋላም ግቢው በልዩ ዓይነት ምንጣፍ ወለሉ የተንቆጠቆጠ እና ያማረ ነበር። ምንጣፉ ላይ ወጥቶ ወደ ግቢው ለመዝለቅም በመጀመሪያ የሚወጡ ሦስት ደረጃዎች ከፊቴ ነበሩ። እኔም ፈረንጁን ተከትዬ ልወጣ የመጀመሪያውን ደረጃ ተራምጄ ሁለተኛውን ልወጣ ስል ኃይለኛ የሕመም ስሜት ተሰማኝ። ወዲያው በቀኜ በኩል ካለ በመስተዋት ብቻ የተሠራ ውብ ቤት አንድ ነጭ ልብስ የለበሰ ረዥም ሰው ወጣ እና ከኔ ጋር የገባውን ፈረንጅ "ሂድ እና ኬዳሞን ዳስሰው!" አለው። እርሱም መጥቶ ዳሰሰኝ። እኔም መጥቶ በዳሰሰኝ ቅጽበት ከሕመሜ ተፈወስኩ።

ከዚያም ተራምጄ ወደ ምንጣፉ ወጣሁ እና ወደ ግቢው ዘለቅሁ። ከመስታወቱ ቤት በስተጀርባ ስደርስም አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ። ይህቺ ሴት በቀኝ እና በግራዋ የተቀመጡ ሁለት ሁለት ልጆች ነበሯት። እኔም በአንድ ባዶ ወንበር ላይ እንድቀመጥ ተደረግሁ እና የሴትየዋን አራት ልጆች "አስተምራቸው" ተባልኩ። ልክ ይህን እንዳየሁም ከነበርኩበት የራዕይ ሰመመን ነቃሁ።

እንደነቃሁም የራሴን ሁኔታ ላይ ፍጹም ድኜ ነበር። ወዲያውኑ ባለቤቴን ታደለችን ከነበረችበት ወጥ ቤት አስጠራሁ። "ታደለች ኢየሱስ ዳሰሰኝ ድኛለሁ።" አልኳት። እርሷ ግን 'በቃ ጭራሽ አዕምሮው ተነካ።' ብላ አስባ ብዙም ትኩረት ሳትሰጥ "ጥሩ ነው፣ ጥሩ ነው።" አለችኝ። እኔም "አንቺ ድኛለሁ ነው የምልሽ፤ እመኚኝ ድኛለሁ፤ ከእንግዲህ አራት ልጆችን ለማስተማር ወደ አራት አገራት እሄዳለሁ እመኚኝ ከእንግዲህ አያመኝም።" አልኳት። በእውነትም እግዚአብሔር በዚያች እሁድ ማለዳ ሙሉ በሙሉ ፈወሰኝ። በኋላ እንደሰማሁትም በዚያው ተመሳሳይ ሰዓት የጌጃ ምዕመናን በሙሉ ስለ እኔ በጌታ ፊት እንባቸውን እያፈሰሱ በመጸለይ ላይ ነበሩ።

ያን ዕለት ፍጹም ጤነኛ ሆኜ ተነሳሁና እግዚአብሔር በራእይ እንዳሳየኝ ይህ በተከሰተ በ15ኛው ቀን በዚያው በመጋቢት ወር ወደ ፊንላንድ ለአገልግሎት አመራሁ። ከጉዞዬ በፊትም አስቀድሜ እግዚአብሔር በጸሎታቸው እንዲፈውሰኝ ወደ ማለዱት የጌጃ ምዕመናን ሄጄ "እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ሰምቶ ፈወሰኝ።" በማለት እግዚአብሔር የሠራውን መሰከርኩላቸው።

በእውነት እግዚአብሔር ድንቅ አምላክ ነው፤ ለእርሱ የማይቻል ምንም ነገር የለም። እርሱ ፍጹም ታማኝ አምላክ ነው፤ አሳይቶ አይነሳም፤ ተናግሮም አያስቀርም። እኔም እግዚአብሔር በራዕይ እንዳሳየኝ ወደ እስካንዴኒቪያን አገሮች አምርቼ ፊንላንድ በአራት ቦታ፣ ኖርዌይ አራት ቦታ፣ ስዊድን ሦስት ቦታ የጌታን የወንጌል ቃል አስተምሬ ወደ አገሬ ተመለስኩ። እግዚአብሔር ወደ አውሮፓ ወስዶኝም ከእንግሊዝ በስተቀር ሌላውን ዋናውን የአውሮፓ ክፍል ሳልሄድ እና ሳላይ ኖሬ በዚህ ጊዜ በእነዚህ ሦስት አገራት ተዘዋውሬ አውሮፓንም እንዳይ አደረገኝ።

በዚህ የእስካንዲኔቪያን አገራት ጉዞዬ ወቅት ጌታ እኔን ከሞት አፋፍ መልሶ ከአልጋ አስነስቶ እንደላከኝ ሁሉ በመንገዴም ተጨማሪ ድንቅን እየሠራ ለአገልግሎት ወደ ተጠራሁበት ምድር አድርሶኛል። በዚህ ጉዞዬ ብቻዬን እንዳልሆን የጠቀመኝ ከኔ ጋር ለአገልግሎት የተጠራው ዘማሪ ታምራት ኃይሌ አብሮኝ መጓዙ ነበር። ከታምራት ጋር ጉዞአችንን ያደረግነውም በዚያ ዘመን በነበረው ጥሩ አማራጭ በሞስኮ በኩል አድርገን ነበር።

ከአዲስ አበባ ሞስኮ ስንደርስም በሞስኮ አውሮፕላን ማረፊያ አንድ አስደንጋጭ ክስተት ተፈጠረ። በወቅቱ ጥብቅ የጸጥታ ቁጥጥር በነበረባት የቀድሞዋ ኮምኒስት ራሺያ ዋና ከተማ ሞስኮ አርፈን ወደ ፊንላንድ ይዞን የሚበርረው አውሮፕላን ላይ መሳፈር ነበረብን። ሆኖም ልክ ሞስኮ አውሮፕላን ማረፊያ ወርደን የይለፍ ወረቀታችንን በምናሳይበት ቦታ ላይ ደረስን። የጸጥታ ሠራተኛው ግን ወደ ሞስኮ የሚያስገባንን የይለፍ ፈቃድ እንዳላገኘን ተናግሮ መሄድ እንደማንችል ገለጸልን።

በዚህ ጊዜ በጭንቀት ተውጠን የአውሮፕላን ማረፊያው የመንገደኞች ማስተናገጃ ውስጥ ቆየን። ላልተወሰኑ ጊዜያት በዚህ መልኩ ቆይተን ሰዓታችንን ስናይ እኛን የሚወስደው አውሮፕላን መሄጃ ሰዓቱ ደርሶ 15 ደቂቃ ብቻ ቀርቶታል። በዚሁ ጊዜ እኔ በተስፋ መቁረጥ የያዝኩትን ፓስፖርት እና የተመታበትን ቪዛ እያገላበጥኩ ሳይ ምንም እንኳን ነገሩ የተጻፈው በእንግሊዘኛ እና በአገሩ ቋንቋ ቢሆንም በሰነዱ ላይ የራይት ምልክት ያየሁ ስለመሰለኝ የይለፍ ፈቃድ የላችሁም ብሎ የከለከለን ፖሊስ ጋ ሄጄ ሰነዱን እና ያለበትን የራይት ምልክት አሳየሁት። ፖሊሱም በድንጋጤ የይለፍ ፈቃድ እንዳለን በመስማማት በጥድፊያ ወደ አውሮፕላን እንድንገባ አድርጎን አውሮፕላኑ ሳያመልጠን በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ብቻ ወደ ፊንላንድ መጓዝ ቻልን።

በእነዚህ አገራት በነበረኝ የሁለት ወራት ቆይታ ጊዜም ብዙ ኢትዮጵያውያንን እያገኘሁ ሳገለግል ቆየሁ። ብዙ እኔን የሚያውቁ ሰዎችንም አገኘሁ።

በዚሁ ጊዜ እኔን ከድሮ ጀምሮ የምታውቅ አንዲት እህት ጋር የነበረኝ ቆይታ በጣም አስደሳች ነበር።

ይህቺ እህት አባቷ የዱራሜ ከተማ ተወላጅ ሲሆኑ እናቷ ግን የእኛ አገር ሰው ነበረች። እናም ከእኛ ጋር ትልቅ ቅርርብ ያለንና እንደ አንድ ቤተሰብ የምንተያይ ሰዎች ነበርን። እኔ እና ቤተሰቦቼ ከእርሷ አያቶች ጋር አብረን እየበላንና እየጠጣን በአንድነት ብዙ ዓመታት አሳልፈናል። እኔ ስዊድን በሄድኩበት ጊዜም እርሷ ስዊድናዊ ባል አግብታ እዚያው ትኖር ነበር። የእኔን ወደዚያ መሄድ ስትሰማም 'አጎቴ ይመጣል' ብላ ለሰው ሁሉ ነግራ በጉጉት ትጠብቀኝ ነበር።

እኔ ስዊድን ከደረስኩ በኋላም በጣም ተደስታ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገችልኝ። ይሁን እና ቤታቸው ውስጥ በእንግድነት በቆየሁበት ጊዜ በመሳው የአውሮፓ ምድር እና በስዊድንም ጭምር እየሆነ እንዳለው ባለቤቷ ጠንካራ እማኝ አልነበረም። ስለሆነም በ15 ቀናት ቆይታዬ በደንብ አድርጌ የደህንነት ትምህርት አስተምሬአቸው እኔም ሆንኩ እነርሱ መልካም ጊዜ አሳልፈን ተለያየን።

ይህቺ እህትም ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ ጊዜ ጀምሮ እየደወለች ያንን መልካም ጊዜ እያስታወሰች እርሷም ሆነ ባለቤቷ እንዴት በእምነት እንደጠነከሩ ትነግረኛለች። አንዳንድ ጊዜም ስጦታዎች ሁሉ ትልክልኛለች። ከዚህም ሁሉ ባሻገር እኔ በሄድኩበት ጊዜ እግዚአብሔር የዘራሁትን የወንጌል ቅንጣት ዘር አሳድጎ ያኔ የተወለደች ልጃቸው ዛሬ በዚያ ወንጌል እየሞተ ባለበት ምድር፤ ወጣቶች የእግዚአብሔርን መኖር እንኳን በረሱበት ዘመን ጌታን የምትወድ ትልቅ አገልጋይ ሆናለች። እንደ የሰናፍጭ ቅንጣት የሆነችው የእግዚአብሔር መንግስት እውነትም ሁል ጊዜ የምታድግ እንደሆነች በስዊድን ባሳለፍኩት የ15 ቀናት ቆይታዬ የታየው ፍሬ ያስታውሰኛል።

በተቀሩት የስዊድን ጎረቤት ሃገራትም እንዲሁ በዚያ ምድር በስደት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተተከሉ አነስተኛ አባላት ባላቸው ቤተ ክርስቲያናት መካከል በጥሩ ሁኔታ ጌታን አገልግዬ ደስ ተሰኝቼ ተመልሻለሁ። እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ነው። ለሞት ታስቤ የነበረውን ተስፋ የተቆረጠብኝ ሰው ራሱ ዳስሶ አስነስቶ "አስተምራቸው" ብሎ እንዳዘዘኝ ሄጄ እንዳስተምርና ፍሬም እንዳፈራለት አደረገኝ። ስሙ ይባረክ!

# ምዕራፍ ፴፩

# ኅብረት እና መቀባበል ለታላቅ ስኬት

## እንደ አንድ ሰው ነበርን

ኬዳሞ በ1965 ዓ.ም የጌኛ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ለመቀላቀል ሲወስኑ በጊዜው ቀልባቸውን ከሳቧቸው ነገሮች አንዱ በዚያች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አባላት ብቻ በነበራት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተመለከቱት የምዕመናንና በተለይ ደግሞ የመሪዎቿ አንድነት እና ፍቅር ነበር። በጊዜው የተለያዩ ሙያዎች የነበሯቸው በልዩ ልዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚያገለግሉ አዲስ አበቤዎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች እና መሪዎች በአብዛኛው ከወገኖቻቸውና ከዘመዶቻቸው መካከል ወንጌልን አምነው የተለዩ ነበሩ። አንዳንዶቹም ዘመዶቻቸውን ራቅ ባሉ የክፍለ አገር ከተሞች እና ገጠራማ ቀበሌዎች በመተው አዲስ አበባ በብቸኝነት የሚኖሩ ነበሩ። እነዚሁ ጌኛ የተሰበሰቡ አገልጋይ መሪዎች የፈጠሩትን ኅብረትም በየጊዜው ከልዩ ልዩ ስፍራ የሚመጡ እና አዳዲስ ጌታን አምነው የሚቀላቀሉ መሰል የወንጌሉ ጽኑ አማኝ ተከታዮች አጠናከሩት እና ኅብረታቸው እያደገ ሄደ።

ከእነዚሁ የዚህ ጠንካራ ኅብረት መስራች-የጌኛ ቀደምት አባላት መካከል አቶ ላቀው ተሰማ እና ወ/ሮ መንበረ፣ አቶ ወልደ አምላክ ዲኬ እና ወ/ሮ ወተቴ፣ አቶ ጥላሁን ኃይሌ እና ወ/ሮ አልማዝ በቀለ፣ አቶ ሙላቱ ታዬ እና ወ/ሮ ቀለሚ ኃይሌ፣ አቶ ብርሃኑ ደረሰ እና ወ/ሮ ፈትለ፤ አቶ ተስፋዬ ባህታ እና ሲ/ር ኤልሳቤጥ ፤ አቶ አዱኛ በዳዳ እና ወ/ሮ ቆንጂት ዲኬ፤ አቶ ሙሉጌታ ኃ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ ብርውሃ፤ አቶ ደምሴ ማዴ እና ወ/ሮ አበበች፤ ዶ/ር ሙላቱ ባፋ እና ወ/ሮ አሰሜ፤ ጀነራል በቀለ ነዲ እና ባለቤታቸው፣ አቶ ጌታቸው ወ/ገብርኤል እና ወ/ሮ ጸሓይነሽ፤ አቶ አሰማየሁ ጎሹ እና ወ/ሮ እቴነሽ፣ ሻለቃ ታደሰ እና ወ/ሮ አልማዝ፤ አቶ ሽመልስ ወዳጆ እና ሲ/ር አልማዝ፤ አቶ ሙሉጌታ እና ወ/ሮ ማጫሽ፤ አቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል እና ወ/ሮ ሰብለ፣ ወንጌላዊ ኬዳሞ እና ወ/ሮ ታደለች እንዲሁም ሌሎችም ነበሩ።

እነዚህ በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራዎች እና የግል ኃላፊነቶች ተጠምደው አገር የሚያገለግሉ ወገኖች ቤተ ክርስቲያናቸውን ከራሳቸው በላይ ይወድዱ ነበር። በብዙ

*ዋጋ መክፈል ከፋውን ዘመን በማለፍ፣ የጌጃ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በመላው አዲስ አበባ በቃለ ሕይወትም ሆነ በመላው አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ጉልህ ሚና እንዲኖራት አደረጉ።*

*ወ/ሮ ኬዳሞ በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ሲመሩ እነዚህ አገልጋዮች በወቅቱ ያሳዩትን ቆራጥነት እና መሰጠት ሲያስታውሱ በጣም ይደነቃሉ። ቤተ ክርስቲያን በሚያስፈልጋት ሁሉ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ ራሳቸውን ሰጥተው ቀድመው ለመገኘት ይጥሩ ነበር። ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ሲደክሙና በአገልግሎት ጉዳይ ላይ ሲመክሩ እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ድረስ ሁሉ ይቆዩ ነበር። አንዳንዴም ከትምህርት ቤት ያወጧቸውን ልጆቻቸውን ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ረስተዋቸው በጣም ሲያመሹ ኬዳሞ ልጆቹን መሰብሰባቸውን ያስታውሳሉ።*

*በኬዳሞ የግል ሕይወትም ይህ የጠነከረ የአማኞች ኅብረት ወንጌላዊው ወደ አዲስ አበባ ከመጡ ጀምሮ የተቀላቀሉት ስለሆነ በአገልግሎታቸው የታየውን ታላቅ ስኬት እንደ አንድ ዋና ነገር ይቆጥሩታል። ኅብረቱ በቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ ለመተጋገዝም ስንዝር ክፍተት አሊያም ጠብታ ሽንቁር የሌለበት ነበር። ስለሆነም ስለዚህ ኅብረት ወንጌላዊው እንዲህ ይላሉ፦*

----------------------------//----------------------------

ይህ እግዚአብሔር በጌጃ ቃለ ሕይወት የሰጠን ኅብረት እንደ አንድ ሰው አንድ ሆኖ የቆመ ነበር። ይህን መሰሉ አስደሳች እና ጠንካራ ኅብረት እንዲመሠረት የረዳንም የኮምኒዝም ስርዓት አራማጁ ደርግ ነው። በዚያ አማኞች (በተለይ በአዲስ አበባ) በጣም ባልበዙበት ዘመን አማኝ የነበረ ሁሉ የእውነት እንደ ወንድም እና እህት ይተያይ ነበር።

እኔ ወደ ጌጃ ስመጣም በመሪዎች መካከል ያየሁት ይህንኑ ነበር። ከዚህ በኋላም ዘመኑ እየከፋ ሲሄድ ኅብረቱም ይበልጥ እየጠበቀ እና እየጠነከረ ይመጣ ጀመር። ከስደቱ መባባስ የተነሳ የነበረው ሁኔታ አስፈሪ ስለነበር ሁላችንም እርስ በርስ እንድንመካከርና እንድንደጋገፍ አደርጎን አንድ ላይ እንጸልይ ነበር። ወንዶች በአንድ ላይ፣ ሴቶች በአንድ ላይ፣ ለየብቻ፣ ደግሞም ሁላችንም በጋራ፤ በየተራ በየቤታችን እየተሰባሰብን በመጸለይ ነበር ኅብረቱን የጀመርነው። ከዚያም መደበኛና ጠንካራ ኅብረት ሆኖ ለአያሌ ዓመታት (የደርግ መንግስት ወድቆም ጭምር) በወር አንድ ጊዜ በየቤቱ እየዞረ ኅብረቱ ሲካሄድ ቆይቷል።

በኅብረታችንም ላይ ከዚህ በፊት ተረኛ በሆነው ቤተሰብ ቤት ሻይ፣ ቡናና ቆሎ ይቀርብና እርሱን እየተቃመስን በብዙ ጉዳይ ላይ ውይይት እና ምክክር እናካሂዳለን። ብዙ በመቆየታችንና ጌታን በመውደድ ስለ ወንጌል በመቅናታችንም በመካከላችን

ምስጢር የሌለ ሲሆን የማይነሳ ጉዳይም አልነበረም። ሁሉን አንስተን እየተወያየን በሁሉ ጉዳይ ላይም አብረን እንጸልያለን።

ያ መተማመን እና መቀራረባችን ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እና እድገት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዳችን የግል ሕይወት ዙሪያም ይንጸባረቅ ነበር። እስከ ዛሬ ድረስም በመካከላችን ፍጹም መተማመን በመኖሩ ማንኛው የግል ጉዳይ ለመጸለይ አንፈራም። አንድ ስለሆንንም የአንዱ መከራ የሁላችንም የአንዱ ደስታም የሁላችንም ደስታ ነበረ። ከዚህ ፍጹም የሆነ ኅብረታችን የተነሳ እስከ ዛሬ ድረስ የአንድነት መንፈስ አለን። ይኸው መንፈስ ወደ ልጆቻችን ተጋብቶም እነርሱም ጠንካራ ኅብረት መስርተው በያሉበት ሆነው ይጠያየቃሉ፤ ይረዳዳሉ።

በተለይ በ17ቱ የደርግ አገዛዝ ዓመታት ዘመን ጌጃ ጠንካራ ሆና በመሀከሏ ክፍፍልና ችግር ሳይገጥማት የውጪም የውስጥም ተጽእኖ ሳያሸንፋት ጠንካራ ሆና እንድትዘልቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የዚህ ኅብረት አባላትም (ሁላችንም ማለት ይቻላል) በየተሰማራንበት ዘርፍ የነበረን የአገልግሎት ተጽእኖ ከጌጃ አልፎ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወትን፤ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን ብሎም አገራችንን ሳይቀር ጠቅሟል። ስለሆነም እግዚአብሔር እኔን ወደ ጌጃ በማምጣት ላለፉት 22 ዓመታትም በብዙ አቅጣጫ ለብዙዎች በረከት እንድሆን ሲያደርገኝ እኔንም ሊባርከኝ ይህ ኅብረት ለጥንካሬዬ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ ጌታ ያመቻቸልኝ ደጋፊ ነበር። እግዚአብሔር አብረውኝ ከጎኔ በመቆም የሚያገለግሉትን በመስጠት የሰጠኝ አደራ እንዲከናወንልኝ ስላደረገ ክብር ለእርሱ ይሁን።

ይህ ኅብረታችን ጌጃ ብዙ አጥቢያዎችን አፍርታ አባላትም ሆኑ መሪዎች ወደ ተለያዩ አጥቢያዎች ሲበታተኑ የመፍረስ አደጋ ተደቅኖባት ነበር። ነገር ግን በጠንካሮቹ የኅብረቱ አባላት በተለይ በነ አቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል፣ በአቶ ጥላሁን ኃይሌ እና በአቶ ሙሉጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ አስተባባሪነት ለኅብረቱ ቀጣይነት መመሪያ አዘጋጅተን ደንብ እና ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲቀጥል ማድረግ ችለናል። በዚህም መሠረት በጥሩ ሁኔታ አንድነታችን እንደተጠበቀ እርስ በርስ እየተጋገዝን ቀጥለናል። በነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም በአቶ ሙላቱ ታዬ ቤት ብዙዎቻችን በተገኘንበት ኅብረቱ የተካሄደ ሲሆን ቀጣዩም በዶ/ር ሙላቱ ባፋ ቤት ተካሂዷል። በመጪዎች ወራትም እንዲሁ ኅብረት ማድረጋችን ጌታ መጥቶ ዘላለማዊ ኅብረታችንን ለሁል ጊዜ ማድረግ እስክንጀምር ድረስ ቀጥሏል።

በዚህ ኅብረታችን መካከልም እግዚአብሔር ባርኮን አሁን ልዘረዝር የማልችላቸውን ብዙ ልጆቻችንን እና ከኛው መካከል አንዳንዶቻችንንም ጭምር የዳርን ሲሆን በሠርግ ዝግጅቶች ላይም ብዙ ተጋግዘናል። እግዚአብሔር እድሜ ሰጥቶን አብረን ኖረን አንዳንዶች ከመካከላችን ሲለዩም እንዲሁ በጋራ የአንዱን ቤተሰብ ኃዘን አዝነን አብረን ተጽናንተናል። ሽመልስ ወዳጆ፣ አቶ ጥላሁን ኃይሌ፣ አቶ ላቀው ተሰማ እና ወ/ሮ ታደለች ከኛ ተለይተው ወደ ጌታ ሲሄዱ በጋራ አዝነን የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደረግን

ሲሆን ባለቤቴ ወ/ሮ ታደለች በሞት በተለየችን ጊዜም በኃዘን ጊዜዬ ሁሉን ነገር ያደረገው ይኸው ኅብረት ነበር።

ደንብ እና መመሪያ ካበጀንለት ጊዜ ጀምሮም ኅብረቱ የራሱ ድንኳን፣ ወንበር የመመገቢያና መጠጫ ቁሳቁሶች ስላለው በደንብ ተደራጅቷል። ስለሆነም በችግርም ሆነ በደስታ ጊዜ ዕቃ በመፈለግ አንቸገርም። እኔም እግዚአብሔር ስለመሰረተው ኅብረት የጀመርኩትን ትረካ በዚሁ ላጠቃልል እና የዚህ ኅብረት አባል የነበረውን ሽመልስ ወዳጆን ሕይወት አንስቼ ይህን ምዕራፍ ላጠናቅቅ።

## የአስር ሰው ጭንቅላት የነበረው ሽመልስ ወዳጆ

ወንጌላዊ ሽመልስ ወዳጆ እኔ ወደ ጌጃ ስመጣ በዚያ አልነበረም። በኋላ ግን አብሮኝ ያገለግል የነበረው ከበደ በልሁ ወደ አሜሪካ በመሄዱ ሽመልስ ከጆማ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ተመርቆ ከኔ ጋር የጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተክርስቲያን ወንጌላዊ ሆነ። እኔ ሽመልስን ጌጃ ከጎኔ በአገልጋይነት ተሰልፎ በማየቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ከኔ ጋር ሲያገለግል ቆይቶ በኋላ የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት የኢትዮጵያ አስተባባሪ ሆነ። ይሁንና ከጌጃ የሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ቢለቅቅም ወደ ጌታ እስከሄደበት ዕለት ድረስ በጌጃም ሆነ በኮተቤ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በአባልነት እና በአገልጋይ መሪነት በትጋት ሲያገለግል ቆይቷል።

ሽመልስ ወዳጆ ትዳር ለመያዝ በተነሳበት ጊዜ ከላይ ያነሳሁት የኛ ኅብረት ትልቅ ሚና ነበረው። ሁላችንም እንደ አንድ ሰው ሆነን የሽመልስን ደስታ የራሳችን አድርገን ተንቀሳቅሰናል። ሽመልስ ሲ/ር አልማዝን ሊያገባ ባሰበ ጊዜ በዚያ በደርግ ዘመን ትልቅ የሠርግ ስነ ሥርዓት ለማካሄድ አቅዶ ነበር።

በዚህ ጊዜ ኅብረታችን እንደተለመደው ግዴታውን ሊወጣ እንቅስቃሴ ጀምሮ ነበር። በኅብረቱ የተለመደ አካሄድ መሠረት አንድ ሠርግ ሲኖር አስፈላጊው ነገር በባለ ጉዳዩ የሚሸፈን ቢሆንም እንኳን ሥራውን በሙሉ ወንዶቹ የወንዱን ሴቶቹም የሴቱን ተከፋፍለው ሁሉም ወደየ ሥራው ይገባል። ስለሆነም በሽመልስ ሠርግ ምን ምን መደረግ እንዳለበት በጋራ ለማቀድ በእርሱ ቤት ሁላችንም ተሰባሰብን። በዚህ ጊዜ ሽመልስ እቅዱን ይፋ ሲያደርግ ቤቱ ለ500 ሰው የምሳ ግብዣ አዘጋጅቶ ሊጠራ እንዳሰበ ነገረን።

ይህን ስንሰማ ብዙዎች የኅብረቱ አባላት ደነገጥን። እኔም "ሽመልስ፦ አንተ ብዙ ወዳጆች እና ደጋፊዎች ስላሉህ ይህንን ማድረግ ትችላለህ። ደግሞም አንተ ለብዙዎች ምሳሌ ነህ። ይሁንና ይህን ታላቅ የሠርግ ስነ ሥርዓት ብታካሂድ ለሌሎች ምን ታስተምራለህ? ሰዉ ሊያገባ እየፈለገ እንዳንተ መደገስ ስለማይችል ሳያገባ ሊቀር ነውን?" ብዬ ጠየቅሁት።

ሽመልስም አስተዋይ ሰው ስለነበረ ወዲያው ነገሩን ወደ እኔ መልሶ "ጋሼ ኬዳሞ አንተ እኮ ለእኔ አባቴ ነህና አንተ ያልከውን እቀበላለሁ። እሺ አንተስ ምን ትላለህ?" አለኝ። እኔም አሰብኩ እና "በቃ 500 ሰው ቤተ ክርስቲያን ይጠራና እዚያ ቀለል ያለ የኮክቴል ግብዣ ይደረግ። ወደ ቤት 150 ሰው ብቻ ይጠራና ለእነርሱ የሚሆን ምሳ ቢዘጋጅ ይህ በቂ ነው።" አልሁ።

እርሱም ይህንኑ ተቀብሎ ሠርጉ እኔ በመከርኩት መሠረት እንዲሆን አደረገ። የጌጃው ኅብረታችንም ለሠርጉ መደረግ ያለበትን ሁሉ እንደተለመደው ተረባርቦ የሠርጉ ስነ ስርዓት በደማቅ ሁኔታ ተከናወነ።

ይህ የሠርግ ስነ ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ለኅብረታችን ትልቅ ትምህርት ሰጥቶን አለፈ። ከዚህ ሁኔታ በመነሳትም በቤተ ክርስቲያናችን አንድ የሠርግ ስነ ሥርዓት ለማካሄድ የድግሱ ሁኔታ ምን መምሰል አለበት በሚል ጥናት ለማድረግ ወስነን ጥናቱ ተደረገ። ከዚያም የቤተ ክርስቲያን የሠርግ ስነ ሥርዓቶች ሲካሄዱ በሦስት ዓይነት የተመረጡ ደረጃዎች ብቻ እንዲሆን ተወሰነ።

በውሳኔው መሠረትም አንድ ሠርግ የሚያዘጋጅ ሰው የሚደግሰው ድግስ እንደ የኢኮኖሚ አቅሙ ሁኔታ እንዲሆንና ድግሱን በተቻለ መጠን ከአቅሙ በላይ እንዳያደርግ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መለስተኛ አቅም ያለው ከሆነ በቤቱ ከ35-50 ሰው ብቻ በመጥራት ምግብ ሲያዘጋጅ ቀሪውን በቤተ ክርስቲያን የኮክቴል ግብዣ አካሂዶ ሠርጉን እንዲያከናውን ሲሆን ሦስተኛው ዓይነት ደግሞ ምንም ገንዘብ ከሌላቸው ሠርጉ ሙሉ በሙሉ በቤተ ክርስቲያን ስነ ሥርዓት ለታዳሚው ኩኪስ እና ለስላሳ ብቻ የሚቀርብበት እንዲሆን ተደረገ። ይህ ውሳኔ ጠቃሚ ስለነበረም በቤተ ክርስቲያን ሰው ሳይጨነቅ ሠርጉን በነጻነት እያካሄደ ኖረናል።

ሽመልስ ወዳጄንም በዚህ መልኩ ድረነው እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ የኅብረታችን አባል እንደሆነ ኖረ። ከዚህ ወንድም ጋር በተያያዘ በተለይ ሁለታችን አብረን በአንድ ቤተ ክርስቲያን በሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት ዓመታትን ስላሳለፍን ብዙ የጋራ ገጠመኞች ነበሩን።

በዚህ አጋጣሚ ሽመልስ የራሱን መኖሪያ ቤት የሠራበትን ከኔ ጋር የተያያዘ አንድ ታሪክ ላንሳ። በዚያ ዘመን መንግስት 500 ብር ብቻ እያስከፈለ ቤት ለሌላቸው 500 ካሬ ሜትር ቦታ ይመራ ነበር። በጊዜው ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ለቦሌ ቅርብ በሆነ ቦታ ላይ ያለው የገርጂ አካባቢ ስለነበር እነ ሽመልስ ወዳጆ፣ ጌታቸው ወ/ገብርኤል፣ አለማየሁ ጎሹ እና ሌሎችም የኛ ቤተ ክርስቲያን አባላት በጋራ በዚሁ አካባቢ ቦታ ጠየቁ። ማዘጋጃ ቤቱም ቦታውን ሊሰጣቸው ተስፋ ሲሰጣቸው ቆይቶ በመጨረሻ በአንድ ነገር አመካኝቶ ሳይሰጣቸው ቀረ። ይህን ጊዜም ጠያቂዎቹ ሌላ ቦታ አግኝተው ለመመራት ሌላ አማራጭ እና ሌላ ቦታ የሚመራበት አካባቢ ያፈላልጉ ጀመር።

ሽመልስም ቤት የሚሠራበትን ቦታ ሳያገኝ ለሥልጠና ወደ ናይሮቢ ሄደ። በዚህ ጊዜ እኔ ኮተቤ አካባቢ ቤት የሠራ የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነው አቶ ተክለሥላሴ ቲማሞን ልጎበኝ ወደ ኮተቤ ሄድኩ።

በዚያ ጊዜ ኮተቤ አካባቢ ራቅ ራቅ ብለው ከሚገኙት ጥቂት የመንግስት ተቋማት በስተቀር አብዛኛው በሰው ያልተያዘ እልም ያለ ጫካ ነበር። አቶ ተክሌ ቤት በሠራበት ቦታም ከእርሱ ሌላ አንድ ሰው ከሠራው ቤት ውጪ አካባቢው ለጥ ያለ ያልተያዘ ሜዳ ነበር። በዚህ ጊዜ እኔም አቶ ጸጋዬ የሚባል የቤተ ክርስቲያናችን አባል እዚያ ለመመራት እያሰበ ስለነበር ቦታውን ካየሁ በኋላ "እኔ እግዚአብሔር ጥሩ ቤት ባይሰጠኝ ኖሮ እዚህ መጥቼ ነበር የምመራው!" አልኩት። ወዲያውም የራሱን ቦታ ያላገኘውን የአገልግሎት አጋሬን ሽመልስ ወዳጄን አስታወስኩና እዚያ ከተከለለው ቦታ አንዱን መርጬ "እኔ በቃ ሽመልስ ከኬንያ እስኪመጣ ድረስ ይህቺን ቦታ ተመርቻለሁ። ሽመልስ መጥቶ ቦታውን ከወደደው የእርሱ ይሆናል። እርሱ አልፈልገውም ካለ ደግሞ ለሌላ ሰው ትሰጡታላችሁ" በማለት ቦታውን ሸንሽነው እየተካፈሉ ለነበሩት ለነ አቶ ጸጋዬ ነገርኳቸው።

ሽመልስ ከናይሮቢ ከተመለሰ በኋላም ከኔ ጋር እንደተገናኘን በመጀመሪያ ወደ ቢሮ ገብተን ጸለይን። ከዚያም "ባንተ ስም ቦታ ተመርቻለሁ።" ብዬ ነገርኩት። በዚያ ወቅት ያጠራቀመው ዘጠኝ ሺህ ብር እንደነበረው አውቅ ስለነበርም ኮተቤ የያዝኩለት ቦታ ብዙ ዛፍ ስላለው እዚያው ጭቃ ለማቡካትም ቀላል ስለነበር "ባለህ ዘጠኝ ሺህ ብር አንተ ቆርቆሮ እና ሚስማር ብቻ ግዛ። ከዚያም እዚያው ባለው እንጨት እና አፈር ጭቃ አብኩተህ አንድ ዛኒባ ቤት መሥራት ትችላለህ።" ብዬ መከርኩት።

"በዚህ ላይ እናንተ ሁላችሁም ኮተቤ ቤት ብትሠሩ ጌጃ ያለውን አገልግሎት በሙሉ እዚያው ማስጀመር ትችላላችሁ። እስከዚያ ድረስም (ያኔ ሽመልስ እንደ እኔ ቮልስ ዋገን መኪና ስለነበረው) አንተ በመኪናህ እየተመላለስክ ጌጃ ልታገለግል ትችላለህ" ብዬ ነገርኩት። እርሱም እንደለመደው "ጋሼ ኪዳሞ አንተ እኮ አባቴ ነህ ያልከውን አደርጋለሁ።" አለኝ ደስም አለው። ሄደንም ቦታውን አየነው እና ወድዶት የራሱ አደረገው። ከዚያ በኋላ ከእርሱ ጋር ቤት ሲፈልጉ የነበሩ ሁሉ እዚያ ቤት እየሠሩ ስለገቡ በርካታ የጌጃ አባላት አንድ አካባቢ መኖር ጀመሩ። ይህም በኮተቤ አዲስ አጥቢያ እንዲኖረን የረዳንን አጋጣሚ ፈጠረ።

እኔም ለሽመልስ ብቻ ሳይሆን በቃለ ሕይወት የከባድ መኪና ሹፌር ለነበረው አቶ ኃይሉም ድጋፍ አድርጌያለሁ። ይህ ሰው እኔ በምኖርበት የቫቲካን ኤምባሲ አቅራቢያ ቤት ተከራይቶ ይኖር ስለነበር ለእርሱም ስለ ኮተቤው ቦታ ነገርኩት። አቶ ኃይሉ እኛ አካባቢ ቤት ተከራይቶ እያለ ሁልጊዜ ወደ እኛ ቤት እየመጣ አብረን እግዚአብሔር ለእርሱ ቤት እንዲሰጠው እንጸልይ ነበር። አንድ ቀን ሳገኘው "አንተ በቃ ከዚህ በኋላ እኔን ስለቤት ጸልይልኝ አትበል። ኮተቤ ሂድ እና ቦታ ተመራ፤ እንደውም (እርሱ ብዙ ጊዜ ከባድ መኪና ይዞ ወደ ሰሜን ይጓዝ ስለነበር) ለክፍለ ሃገር ጉዞህም ቦታው

መንገድ ዳር ያለ ስለሆነ ጥሩ ነው፤ እዚያው ቤት ሠርተህ ግባ።" ብዬ መከርኩት። እርሱም እዚያው ሄዶ አስፓልት መንገድ ዳር ቦታ ተመርቶ ቤት ሠርቶ ገባ።

ሽመልስ ወዳጆ ጌጃን ለቅቆ ታላቁ ተልዕኮን ማገልገል እስኪጀምር ድረስ ከእኔ ጋር ጌጃ ብዙ አገልግለናል። ሁለታችንም ጌጃ በነበረን ቆይታም ከውጪ ለሚያየን ሰው በጣም ጠበኞች ልንመስል እስክንችል ድረስ እየተሟገትን የምንሠራ በአንድ ጉዳይ ላይ በቀላሉ ለመተማመን የሚቸግረን ኃይለኞች ነበርን። እኔና እርሱ በአንድ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ምክክር ስናደርግ ያየ ሰው ሁለተኛ ተመልሰን የምንገናኝ ላይመስለው ይችላል። ሁል ጊዜ ልናስፈጽመው በተነሳነው ዓላማ ዙሪያ ስንሟገት እጅጌአችንን ሰብስበን ተፋጥጠን በጣም በኃይል እየተነጋገርን ነበር። ነገር ግን በንግግራችን ሁሉ ሽመልስ ሃሳቤን እንጂ እኔን ሳይነካ እኔም ሃሳቡን እንጂ ሽመልስን ሳልነካ እንለያያለን።

እኔ እና እርሱ በአቋማችን ጽኑ ስለነበርን ሳናምንበት በቀላሉ አንድን ነገር ስለማንቀበል፤ አገልግሎቱ ደግሞ በጋራ የምንሠራው ስለነበር በብዙ የሃሳብ ልዩነቶቻችን ላይ ለበርካታ ጊዜያት ኃይለኛ ሙግቶች አድርገናል። ለወንጌል ቀንቶ እንደዚያ ብዙ ማሰብ፣ መወያየት እና መሟገት እንዴት ያስደስታል?! በዚያ ላይ ሁል ጊዜ አንዳችን ለሌላው እግዚአብሔር የሰጠውን ጸጋ ስለምናውቅ በጣም እንከባበራለን።

ጌጃ አባላትን እና ያመኑትን የምናስተምረውም ሁለታችንም የተለያዩ ትምህርቶች ነበሩን። እኔ ባለሃያ ክፍል የደህንነት እና የወንጌል ተልእኮ ትምህርት የማስተማሪያ መምሪያ ያዘጋጀሁ ሲሆን ሽመልስ ደግሞ ታላቁ ተልእኮ የሚል የማስተማሪያ መምሪያ ነበረው። ይህንን ያዘጋጀውን የማስተማሪያ ሰነድም በታላቁ ተልእኮ አገልግሎት አማካኝነት ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲያገለግል አድርጎት ነበር።

ሽመልስ ከጌጃ ባሻገር የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የወጣቶችን አገልግሎት (ያኔ ዘመኑ አስከፊ ስለነበር) የዲያቆናት አገልግሎት ብላ ሳንጋኖ ስታስጀምር እርሱ የላቀ የአመራር እና የአገልግሎት ሚና ከነበራቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ወጣት መሪዎች አንዱ ነበር። ከዚያም የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ሲቋቋም እርሱ በአስተባባሪነት ለመላው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በሙሉ በረከት የሆነ አገልግሎት በመስጠት ብዙ ውለታ ውሏል።

በዚሁ መተሳሰብና መከባበር እየኖርን ቆይተን ሽመልስ ለሥልጠና ወደ ናይሮቢ ሄዶ ነበር። እኔ በቤቴ የተለመደ የሌሊት ጸሎቴን እያደረስኩ እያለም አንድ ራእይ አየሁ። ያየሁት ራእይም ሽመልስ በነበረበት የሰው አገር ውሾች ሲነክሱት ነበር። እርሱ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣም ወዲያውኑ ካለበት ጠርቼ እኔ ቢሮ እንዲመጣ አደረግሁ እና ያየሁትን ህልም ነገርኩት። እርሱም ያለበትን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ዘርዝሮ ባይነግረኝም ብዙ ችግር እንዳለበትና እንድጸልይለት ነግሮኝ ተለያየን። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም አስተዋዩና እርቆ አሳቢው አገልጋይ ሽመልስ ወዳጆ ታሞ አልጋ ላይ ዋለ።

በኋላም ሕመሙ ጸንቶበት ባልቻ አባ ነፍሶ ሆስፒታል እንዲተኛ ተደረገ። እኔም እዚያው ድረስ ሄጄ ጠየቅሁት። ናይሮቢ ያለፈበትን አሳዛኝና ፈታኝ ሁኔታ ጨምሮ በወቅቱ የነበረበትን የጤና መቃወስ ነግሮኝ ብዙ ተጫዋወትን፤ ብዙም ተማከርን። ድንገትም ሽመልስ በተኛበት አልጋ ላይ ቁጭ እንዳለ አስብ አደረገ እና "ጋሽ ኬዳሞ አንተ እኮ እግዚአብሔር የሰጠህ እውቀት ብዙ በመሆኑ የክብር ዶክትሬት ሊሰጥህ ይገባል።" አለኝ።

እኔም "የክብር ዶክትሬት ቢኖርም ምንም አይጨምርም። አለመኖሩም ደግሞ ምንም አልቀነሰብኝም። ታዲያ ምን ይጠቅመኛል?" አልኩት። እርሱም በምላሹ ሲስቅ ቆየ እና "አይ ያስፈልግሃል" አለኝ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም እኔ ሁል ጊዜ እንደምናገርለት የአስር ሰው ጭንቅላት ያለው የወንጌል አገልጋይ ሽመልስ ወዳጆ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ኅብረታችንም እንደተለመደው የተወደደ ወንድማችንን በአንድነት ሁሉን ተወጥተን ወደ አገለገለው ጌታ በክብር ሸኘነው።

በደጉ ጊዜ ከሽመልስ ጋር ቢሮ ተቀምጠን ስንጫዋወት ሞት ለኛ ድል እንጂ ሽንፈት አለመሆኑን በማንሳት ሽመልስ ደግሞ የብዙ ዓመት ታናሼ ስለነበር "በኔ ቀብር ላይ አንተ ነጭ ልብስ ለብሰህ ትሰብካለህ" ብዬው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የፈቀደው ሆነና እኔ እራሴ በብዙ ኃዘን በወዳጆ ቀብር ላይ ለመስበክ ተገደድኩ። ከእርሱ ጋር ተነጋግረን የነበረውንም በቀብሩ ላይ ለነበረው ታዳሚ ተናገርኩ። የሽመልስ ወዳጆን ሞት ሳስብ ጌጃ፣ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እና ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት አንድ ታላቅ አገልጋይ ያለጊዜው እንዳጣ አስባለሁ። እኔ ጌጃን በለቀቅኩበት ወቅትም ተተኪ በማሰብ ስጨነቅ ሽመልስ ቢኖር እንዴት የሚያሳርፍ ሰው እንደነበር እያሰብኩ ነበር። ሽመልስ የእውነት የ10 ሰው ጭንቅላት የነበረው የተሰጠ አገልጋይ ነበር።

# ምዕራፍ ፴፪

# ከጌኛ ... ወደ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት

*ወንጌላዊ ኬዳም በ1981 ዓ.ም እግዚአብሔር ለወንጌላዊው "ቃለ ሕይወት ሞተች" ብሎ ከተናገራቸው በኋላ በራሳቸው ተነሳሽነት የራሳቸውን ቤተክርስቲያኒቱን ህያው የማድረግ እርምጃ ሊራመዱ ሞክረው እግዚአብሔር የእርሱን ጊዜ ቀድመው መሄድ እንደሌለባቸው ተናግሯቸው ነበር። በዚህ የተነሳም ወንጌላዊው በአገሪቱ የመጣው የመንግስት ለውጥ ባስገኘው የእምነት ነጻነት የተነሳ በብዙ ቦታዎች በተከፈተላቸው የአገልግሎት በሮች ማገልገልን ከጌኛው መጋቢያዊ አገልግሎት ጎን ለጎን ተያይዘውታል። እንዲሁም እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ለቃለ ሕይወት ትንሳዔ ወደ ሚሠሩት ሥራ የሚያሰማራበት ጊዜ እስኪመጣ ተተኪ አገልጋዮችን ለቤተክርስቲያን ለማፍራት ዕድሉን ባገኙበት ስፍራ ሁሉ ይዘረጋሉ።*

*ስለሆነም ወንጌላዊው ብዙ ዓመታት ባገለገሉበት እና ጥሩ ተሰሚነት ባተረፉበት ቦቢቾ የነበሩ የቤተክርስቲያን መሪዎችን በሃዲያ ምድር በወቅቱ ከነበሩት 15 ክፍለ ማኅበራት በአጠቃላይ ሁለት ሁለት የወደፊት አገልጋዮች እንዲያዘጋጁ እና እነዚህኑ አገልጋዮች ጊዜ ወስደው ለማስተማር ወሰኑ። በዚህ ጥያቄ መሰረትም በወቅቱ ቦቢቾ ዋና ጸሐፊ በነበረ ደሳለኝ ተሰማ የተባለ ትጉህ አገልጋይ አስተባባሪነት ለ6 ወራት ያህል ተተኪ አገልጋዮቹ በኬዳም እና በሌሎችም ሲማሩ ቆይተው እነርሱን ለማስመረቅ በ1984 ዓ.ም ሄዱ።*

*ወንጌላዊው በዚህ መልኩ እየተጉም እግዚአብሔር የሚያመጣውን ጊዜ ይጠባበቁ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይም ትውስታቸውን እንዲህ በማለት ያወጉታል፦*

-----------------------------//-----------------------------

ቦቢቾ እኔ የሰጠሁትን ምክር ተቀብለው እነዚያን አገልጋዮች እንድናስተምር በማድረጋቸው ቤተ ክርስቲያን በጣም ተጠቅማለች። ዛሬ እነዚያ አገልጋዮች ያኔ በተማሩት ላይ ጨምረው ምሁራን ሆነው በእድሜ በስለው በደንብ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እኔም አሜሪካ ሄጄ በተመለስኩበት ዓመት ይህንኑ በተመሳሳይ መልኩ እንዲያደርጉ፣ ከኔ ጋር አብሮ ጌዴኦ ሄዶ ወንጌል ለሰበከ ለአንድ የቤተ ክርስቲያናችን

ቀጣና መሪ "ከየ ክፍለ ማኅበሩ ሁለት ወይም ሦስት ሰው አሰባስባችሁ ይማሩ። እንተም ለተወሰነ ጊዜ ልታስተምራቸው ትችላለሁ።" በማለት መከርኩ።

እነርሱ ግን ምክሬን ተቀብለው ተግባራዊ ሳያደርጉት ስለቀሩ በዚያ አካባቢ ቤተ ክርስቲያናት ዛሬም ድረስ በመደበኛነት የሚያገለግል የሙሉ ጊዜ አገልጋይ እጥረት አለ። ይህንኑ በተደጋጋሚ ለልዩ ልዩ ኅብረት መሪዎች መክሬ ብዙዎች ተግባራዊ ሳያደርጉት ቀርተው በአገልጋይ እጥረት ሲቸገሩ አይቻለሁ።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ስደት በቆመበት ዘመን ጅማሬ ላይ በጣም ችግር ላይ እየወደቀች ነበር። ከስደቱ በፊት ሲያገለግሉ የነበሩ ትልልቅ አገልጋዮች በእርጅናና በሞት ከአገልግሎት እየወጡና ያሉትም ቢሆን  እየደከሙ ነበር። በደንብ መጽሐፍ ቅዱስ የተማረ ወጣት አገልጋይ ደግሞ ብርቅ ነበረ። ጭራሽ ለብዙ ዓመታት ካድሬ ሆነው እግዚአብሔር የለም ሲሉ የነበሩና በቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገባ ያልተማሩ ግለሰቦች ማገልገል ጀምረዋል።

እኛ በቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮችን ስንቀበል በመጀመሪያ እውነተኛ ጥሪ በመቀጠልም ስጦታ እንዳላቸው እየመረመርን ነበር። ብዙዎች እኔ ጥሪ አለኝ ብለው መጥተው የነበረ ቢሆንም እኛም "እንዴት ነው ጥሪው የመጣልህ? መቼ? የት? በምን ዓይነት ሁኔታ?" ብለን እንመረምራለን። ከዚያም "በጣም ጥሩ ነው በደንብ ተዘጋጅ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ግባ" እንላቸዋለን። አንድ ሰው በመጀመሪያ ይጠራል፤ በመቀጠል ይዘጋጃል፤ ከዚያ በኋላ ነው ወደ አገልግሎት የሚገባው።

ኢየሱስም በዚህ መልኩ ነበር ሐዋርያትን ያዘጋጀው። በመጀመሪያ ጠራቸው፤ ከዚያ ደቀ መዛሙርቱ ሆኑ፤ ከዚያም ከእርሱ ተምረው ተዘጋጁ። በዚህ ዓይነት ብዙ አገልጋዮችን ማፍራት ቢቻልም በዚያ ወቅት ግን ይህ አልነበረም እየተደረገ የነበረው።

ይህ አስቸጋሪ ለአገልግሎት የማይመች ሁኔታ ወደ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ገብቶም አንዳንድ ሽማግሌዎች የሚፈልጓቸውን ሰዎች ረዳት አገልጋይ እየተባሉ እንዲገቡ አስደረጉ። ሴቶችና ወንዶች እንዲገቡ ተወስኖ ሰባት ሰዎች የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆነው ማገልገል ጀመሩ። ከእነዚህም መካከል እነ አረጋሽ ሹጉጤ፣ እነ ቬኑስ አሁኑ፣ እና አብይ ... ነበሩበት። አረጋሽ የኔ ረዳት የነበረች ሲሆን እርሷ ስትቀየር ደግሞ ቬኑስ ረዳቴ ሆናለች። ተስፋዬ በቀለ የሚባል አገልጋይ ደግሞ የሽመልስ ወዳጆ ረዳት ሆኖ ሲያገለግል ነበር። እነዚህ ሁሉ ሲገቡም አገባባቸው ያላቸው ጥሪ፣ ስጦታ እና መስጠት በደንብ ሳይመረመር ነበር። ስለሆነም ከገቡት መካከል አንዳንዶቹ ብቻ በሚገባ ማገልገል ሲችሉ የተቀሩት ግን ዝም ብለው በቦታው ላይ ተቀምጠው ኖሩ እንጂ ውጤታማ አገልግሎት አልሰጡም።

ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሁሉ ሁል ጊዜ አገልጋዮችን ሲቀበሉ የራሳቸውን ፍላጎት ወደ ጎን አድርገው የሚያመጡትን ሰው ለአገልግሎት መጠራቱን፣

ለሚያገለግለው አገልግሎት የሚበቃ ስጦታ እንዳለው እና በሚገባ ተምሮ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ላስጠነቅቃቸው እወዳለሁ። ይህ ካልሆነ ግን አገልግሎቱና አገልጋዩም ራሱ ይጎዳሉ።

እኔም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው እንግዲህ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እና በመላ አገሪቱ እግዚአብሔር ሲልከኝና ከአገርም እየወጣሁ ሳገለግል የቆየሁት። በመላ አገሪቱ ያለውን ችግር በማየትም በአቅሜ ልክ በዓመት ውስጥ በጥቂት ቦታዎች እየተዘዋወርኩ አገለግል ነበር።

## ብሔራዊ ቦርዱ ብሔራዊ ወንጌላዊ እንድሆን ወሰነ

በ1987 ዓ.ም ላይም የዚህን ችግር አሳሳቢነት ያየው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ቦርድ አራት ሰዎች ተመርጠው በዋና ጽ/ቤቱ ስር ሆነው በመላ አገሪቱ እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ ወሰነ። እኔም በጊዜው በዋና ጽ/ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊዎች በነበሩት በአቶ ጥላሁን ኃይሌ እና በአቶ ደምሴ ማጼ ጠቋሚነት ለዚሁ አገልግሎት ከተመረጡት አራት ሰዎች መካከል አንዱ ሆንኩ። ይህንኑ አቶ ጥላሁን ለኔ ሲነግሩኝም "የቤተ ክርስቲያናችን ብሔራዊ ቦርድ አንተ ወደዚህ አገልግሎት እንድትመጣ በሙሉ ድምፅ ነው የተስማማው። የቦርዱ አባላት በአንተ መምጣት እንደተስማሙ በሌላ ነገር እንዲህ ተስማምተው አያውቁም ነበር።" አለኝ። በእርግጥ እኔ በብዙ ቦታ ተዘዋውሬ ሳስተምር ስለነበር ሁሉም ያውቁኝ ነበር ማለት ይቻላል።

በመቀጠልም እኔ ጋር የሚያገለግሉትን ሌሎቹን ለመምረጥ ብዙ ተከራክረው መወሰናቸውን ነገሩኝ። እኔም ይህንኑ ሰምቼ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ተናግሮኝ ለዓመታት የጠበቅሁበት እና በግሌም የጀመርኩት ስለነበር በሃሳቡ ተስማማሁ። ጌጃ የእኔን አገልግሎት የሚረከቡ ተተኪዎች አዘጋጅቼ አስረክቤ መውጣት እንዳለብኝም አሰብኩ እና ተተኪ ሳላገኝ እንዳልሄድ በመስጋቴ ዝውውሩ በጣም አስፈሪ ሆነብኝ።

በመጨረሻም በኔ ቦታ የሚተካ አንድ ሰው እንዲሰጡኝና ለእርሱ የምሠራውን ለሁለት ወራት ያህል አሳይቼ እና አዘጋጅቼ በኋላም ሥራውን አስረክቤው ለመሄድ ለጌጃ የሽማግሌዎች ጉባኤ ጥያቄዬን በደብዳቤ አቀረብኩ። ነገር ግን ከሽማግሌዎች የተሰጠኝ ምላሽ በኔ እምነት ፍጹም ማስተዋል የጎደለው አሳዛኝ ውሳኔ ነበር። የኔ ጥያቄ 'አንድ ሰው ስጡኝ እና እኔ የምጠቀምበትን የአገልግሎት ስልት ላሳየው' የሚል ነበር። እነርሱ ግን እኔን በቀጥታ ወደ ጉባኤያቸው ጠርተው "አንተ የምትሰጠው የተለየ አገልግሎት ምንድን ነው?፣ ሌላ ሰው እንዴት ማገልገል ያቅተዋል?" አሉኝ።

በእውነቱ ይህ ጥያቄ በኔ እይታ ፊጽሞ አግባብነት ያልነበረው ያላዋቂ ጥያቄ ነው። እናም እኔ "ምን ምን እንደማገለግል ለእናንተ በየወሩ በማቀርበው ሪፖርት ታውቃላችሁ። አምስት የአገልግሎት ኃላፊነቶች ያሉኝ ሲሆን የሁሉንም የአፈጻጸም ሪፖርት ታገኛላችሁ። በዚያ ላይ አገልግሎቴን ታውቃላችሁ። እንዴት እንደማገለግል

እና ለአገልግሎቴ ምን ዓይነት ስልት እንደምጠቀም ግን አታውቁም። ጥያቄዬ በኔ ቦታ ትልቅ ሰው መምጣቱ አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት አንድ ኮስማና ምስኪን ሰው ቢመጣም ሊሠራው ይችላል። አቋማችሁ እና እምነታችሁ ይህ ከሆነ ለኔ ነገ ጠዋት ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት የመሸኛ ደብዳቤ ጻፉልኝ።" አልኳቸው። እኔ ለመልቀቅ ፍርኃት ሆኖብኝ የቆየውን ጉዳይም እግዚአብሔር እንድሄድ ሲለቀኝ ፈልጎ ይሆናል ብዬ በቀጥታ ለማቆም ወሰንኩ። እነርሱም በማግስቱ ደብዳቤ ጻፉልኝና ደብዳቤውን ተቀብዬ ወደ ዋና ጽሕፈት ቤት አስገባሁ።

በእግዚአብሔር እርዳታም ጌጃ አጥቢያ ለ22 ዓመታት በብዙ ዋጋ መክፈል እና በብዙ ድል አሳለፍኩ። በዚያ ወቅት እኔ ብለቅቅ አንዳንድ ሽማግሌዎች ሊያደርጉ ያሰቡት ነገር ስለነበር በቀላሉ እንድለቅ ሆነ እንጂ እኔ የአገልግሎት ኃላፊነቶቼን እንኳ ውሰድ ብዬ የማስረክበው ሰው ባለመኖሩ ተጨንቄ ነበር። ያኔ የነበረው የኔ ተተኪ ሽፈራው ፈይሳ ሲሆን እርሱ ደግሞ ያኔ በጥሩ ሁኔታ ማስተማር እንጂ በጥሩ ሁኔታ ለመምራት በቂ ልምድ አልነበረውም። ምናልባት አሁን ቢሆን ሊመራ ይችል ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

## ቀዝቃዛው ሽኝት

ጌጃን ለቅቄ የዋና ጽሕፈት ቤቱ አገልጋይ ስሆን እንደተለመደው የሽኝት ፕሮግራም ተዘጋጅቶልኝ ነበር። በእርግጥ ለአገልግሎት ወደ ዋና ጽሕፈት ቤት መዛወሬ በአንድ ጊዜ ከጌጃ አጥቢያ የሚያርቀኝ ስላልነበር ታላቅ ስንብት የሚያስፈልገው አልነበረም። እኔም በጌጃ አጥቢያ ያፈራኋቸውን እግዚአብሔር የሰጠኝን ወንድሞች፣ እህቶች፣ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ቶሎ ቶሎ ማግኘቱ አስቸጋሪ ስለማይሆን ርቂ እንደምሄድ አልተሰማኝም።

ሆኖም እዚያ የነበሩ ሽማግሌዎች በዚያን ጊዜ እኔ ስለቅ በኔ ቦታ ራሳቸውን ለመተካት ያሰቡ ስለነበሩ የመልቀቁ ሁኔታ እና አካሄዱ በመልካም መንፈስ የተከናወነ አልነበረም። በተለይ ከ22 ዓመት በፊት ወደ ጌጃ ስመጣ ከነበረው የሆሳዕና ሽኝት አንጻር ይህኛው በጣም ቀዝቃዛ ነበር። በቦቢቾ የነበረው አገልግሎቴን ጨርሼ ስሰናበት በተለይ በሆሳእና የተደረገልኝ ሽኝት ዛሬም ድረስ የማልረሳው በመገባ አገልግዬ ከነበረኝ አገልግሎት ስለይ ብዙዎች አልቅሰው የልብ ስሜታቸውን የገለጡበት ስለእኔም ብዙ መልካም ነገሮች የተነገረበት ነበር። እናም የቦቢቾን ሦስት እጥፍ በቆየሁበት እና አጅግ አስደናቂ የአገልግሎት ጊዜ ካሳለፍኩባት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስለይም ሞቅ ያለ ሽኝት እንደሚኖር የሚጠበቅ ነበር።

ሆኖም በጌጃ የተደረገልኝ የሽኝት ፕሮግራም መደበኛው የሽኝት ስጦታ፣ የመሪዎች ንግግርና ጸሎት የተካሄደበት ይሁን እንጂ በወቅቱ በመሪዎች ዘንድ በነበረው ሁኔታ

መቃቃር ተፈጥሮ እና የቀድሞው ፍጹም መቀባበል ቀዝቅዞ ስለነበር ሽኝቱም ባልተፈታ ድባብ እና ቀዝቀዝ ባለ መልኩ የተካሄደ ነበር። ምንም እንኳን ለረጅም ዘመን ያበረከትኩትን አገልግሎት በማሰብ ሰፋ ያለ ዝግጅት ባያደርጉም ስለሰጠሁት አገልግሎት የመባረኪያ እና ስለመጪው አገልግሎቴ የሚጸለይበት ፕሮግራም ቢያዘጋጁም አስቀድሜ እኔ ተተኪ አዘጋጅቼ ለመሄድ ባቀረብኩት ሃሳብ እና እነርሱ ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልገውን አስበው ሃሳቤን ለመቀበል ፈቃደኛ ስላልሆኑ በወቅቱ በነጻነት ሁሉን ለማከናወን የሚያስችል መንፈስ አልነበረም። እኔም የተሰጠኝን ተቀብዬ የምናገረውን ተናግሬ ወደ ቤቴ ሄድኩ። በዋና ጽሕፈት ቤቱ ለምስጠው አገር አቀፍ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት አገልግሎትም ተዘጋጀሁ። በጌጃ አጥቢያቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሳገለግልም ለብዙ ዓመታት እየረዳኝ በብዙ ፍሬ ለባረከኝ አምላኬ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ወደ አዲሱ የአገልግሎት መስክ አመራሁ።

------------------------------//------------------------------

# የሽፍቶች ወረራ ... ከሞት ጋር በስንዝር ርቀት

*ጊዜው 1984 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ አገሪቱ በአዲስ አመራር መተዳደር የጀመረችበት እና የኢትዮጵያ ሁኔታ እና መጻኢ እጣ ፈንታዋ እንኳን ለሕዝቡ ለአዲሶቹ መሪዎቿም በውል ያልለየበት፣ ስጋት፣ ፍርኃት እና ጭንቀት በሰው ሁሉ ላይ የነገሠበት ዘመን ነበር።*

*የቀድሞው ወታደራዊ መንግስት ፈርሶ ለዓመታት ሲያደራጀው የነበረው በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ሠራዊት ከነታጠቀው መሣሪያ በመላ አገሪቱ ተበትኗል። ወደ አዲሱ መንግስት ተጠግቶም የሚኖረው እጣ ፈንታ በቀድሞ ሥራው መቀጠል ሳይሆን የተኃድሶ ስልጠና ወስዶ መበተን መሆኑን በመረዳቱም አብዛኛው የቀድሞ ወታደር በያዘው መሣሪያ እየዘረፈ መብላትን አማራጭ አድርጎ የሕዝቡን ጭንቀት እጥፍ አባብሶታል። በጊዜው ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አስጨናቂ የነበረ ሲሆን በተለይ በምሽት መጓዝ በራስ ላይ አደጋ እንደመጋበዝ ይቆጠር ነበር።*

*በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ዶ/ር ሙላቱ ባፋ፣ አቶ ደምሴ ማዴ፣ አቶ ግርማ ሃናኖ እና ሌሎችም ወንጌላዊ ኬዳሞን ጨምረው በዋና ጽሕፈት ቤቱ ቶዮታ ስቴሽን ዋገን መኪና በቦቢቾ የሚካሄድ የአገልጋዮች ምረቃ ስነ ሥርዓትን በክብር እንግድነት ለመታደም ተጉዘዋል። (በጊዜው በቦቢቾ የአውራጃው የእምነት አባቶች የአገልግሎት ገድል የሚወሳበት ልዩ ኮንፍረንስም ተዘጋጅቶ ስለነበር ዘማሪያን እና በወቅቱ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን በቪዲዮ ቀረጻ ሙያ የሚያገለግለው የወንድማማች ቤተክርስትያን አገልጋይ የሆነው አቶ ሰለሞንም አብሮ ተጉዞ ነበር።) እንዚሁ ፕሮግራሞች*

ተጠናቅቀውም ተጓዦቹ ወደ አዲስ አበባ የመመለሻ ጉዞአቸውን ሊጀምሩ ተነስተዋል። ይሁንና በርከት ብለው የሄዱት የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ባቢቻ ካሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ሲነጋገሩ ወደ አዲስ አበባ የመነሻ ሰዓታቸው እየተጓተተ ሄደ።

በዚሁ ጊዜም ሁል ጊዜ ለጉዞ ሲነሱ ማልዶ መነሳትን፣ አስፈላጊውን መሰናዶ ሁሉ ቶሎ መከወንን እንደሚወዱ የሚነገርላቸው ቆፍጣናው ወንጌላዊ ኬዳሞ በጉዞው መጓተት ቅር ተሰኝተዋል። በተለይ ሰዓቱ ገፍቶ ዕኩለ ቀን ሲቃረብም ወንጌላዊው ሃሳባቸውን ቀይረው ተለይተው ለማደር እና በማግስቱ በሕዝብ ትራንስፖርት ለመመለስ ሁሉ ያመኑቱ ጀመር። በመጨረሻም በዋና ጽ/ቤቱ መሪዎች አደፋፋሪነት እና ጉትጎታ በጣም ከረፈደ በኋላ ተነስተው የሀሳዕና ከተማን ለቅቀው ወደ አዲስ አበባ መጓዝ ጀመሩ።

በዚያ ዘመን ከሀሳዕና አዲስ አበባ የሚወስደው መንገድ አስፓልት ያልገባለት ጥርጊያ የጠጠር መንገድ ስለነበርም እንደዛሬው ከአምስት ሰዓት ባነሰ ማገባደድ የሚቻል አልነበረም እና በመንገድ ላይ እያሉ ጀምበር በመጥለቋ ጉዞው አስፈሪ የጨለማ ጉዞ ሆነ። ሁሉም ከፊት ለፊት ያለችውን አዲስ አበባን ከሩ ሳያጋጥማቸው ለማየት እየተመኙ በስጋት፣ ስጋታቸውንም ለመርሳት የባጥ የቆጡን እያወሩ ይጓዙ ገቡ።

መንገዱ ተገባድዶ አዲስ አበባ ሊገቡ ከ100 ኪ.ሜ በታች ቀራቸው። በድንገት ግን በዚያ አስፈሪ ጨለማ ውስጥ ባትሪ ይዘው መንገድ ዘግተው የቆሙ ፊርጣማ መሣሪያ አንጋቾች ከፊታቸው ገጭ በማለታቸው መኪናቸው ቆመ። እነዚሁ በርካታ ሽፍቶችም በደንብ የታጠቁ እና ወታደራዊ ቁመና ያላቸው ነበሩ። ከርቀት የሚታይ ጉብታ ላይ መትረየስ የደገነ ወታደር አድፍጧል። በቅርብ ያሉትም በሙሉ የታጠቁ ስለነበሩ ጠመንጃቸውን መኪና ውስጥ ባሉት ላይ ወድረዋል።


ወዲያው ሁሉም ከመኪና እንዲወርዱ ታዘዙና ፊታቸውን በአቅራቢያው ወዳለ ቋጥኝ አድርገው እንዲቆሙ ከተደረገ በኋላ መኪናው ተበርብሮ ያላቸው ንብረት ሁሉ ተወሰደ። በኪሳቸው የነበረ ገንዘብም ተፈትሾ ተወሰደና ሁሉም ባዶአቸውን ከቀሩ በኋላ ወደ መኪናቸው እንዲመለሱ ታዘዙ። ከመካከላቸው አንድ የተወሰደበት ዕቃ እንዲመለስለት የጠየቀ ሰው ብቻ የሰደፍ ጡጫ ሲቀምስ ሁሉም ምንም ሳይሆኑ ገብተው ቁጭ አሉ። መኪናው ውስጥ ጋቢና ተቀምጠው መሪ የጨበጡት ዶ/ር ሙላቱ ላይ የጠብመንጃ አፈሙዝ በመደገንም ቀጥ ብለው እንዲያሽከረክሩ ተነገራቸው። ከሽፍቶቹ መካከል አንዱ የጠብመንጃውን አፈሙዝ በአቅራቢያው ወደ ነበረ ድንጋይ አስጠግቶ በጠብመንጃው ውስጥ የነበረውን ጥይት አርከፈከፈበት። ከጠብመንጃ ተኩስ ድምጹ ጋርም ጥይቱ ከድንጋይ ጋር ሲጋጭ የፈጠረው ሰቅጣጭ ድምጽ ተሰማ። በዚሁ ተኩስ ወቅት የጥይቱ ቀለሃ እየተፈናጠረም የመኪናውን አካል ይደበድብ ነበር።

የጥይት ድምፅ መስማት ያልለመዱት ሰላማውያንም በመሸበር መኪናቸውን አስነስተው ወደ አዲስ አበባ ሸመጠጡ።


ትንሽ እንደሄዱም ዝምታውን ሰብረው ነፍሳቸውን ያተረፈላቸውን ጌታ ማመስገንና ስለተወሰደባቸውም ዕቃ በመቆጨት መናገር ጀመሩ። በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ በርካታ (በቅርቡ ከአሜሪካ ያመጧቸውን ሳይቀር) ሙሉ ልብሶች እና የምሽት ልብሶቻቸው መወሰዳቸውን አስታወሱ። ሽፍቶቹ መኪናቸውን ሲያስቆሙአቸው በፍጥነት አውልቀው ጫማቸው ውስጥ ያስቀመጡት ቀለበታቸው ብቻ ሲቀር የነበራቸው ገንዘብም ቤሳ ቤስቲን ሳይቀር ተወስዷል። ከእነዚህ ከተወሰዱባቸው ዕቃዎች ሁሉ በላይ ግን ወንጌላዊውን በጣም የቆጫቸው ንብረት በርካታ መልዕክቶቻቸውን የያዘው የማስታወሻ ደብተራቸው ለሽፍቶቹ ምንም ሳይጠቅም አብሮ መሄዱ ነበር። ወዲያው ቁጭታቸውን አብረዋቸው ለነበሩት መሰል ተዘራፊዎች ተናገሩ። ማስታወሻ ደብተሩ ሳይመለስ በመጥፋቱም አዘኑ።

ይህ ከተፈጸመ ጥቂት ሳምንታት አለፉ፤ ወንጌላዊ ኬዳሞ እና መሰሎቻቸውም የደረሰባቸውን ረስተው አገልግሎት እና ሥራቸውን ቀጠሉ። አንድ ዕለት ኬዳሞ በቢሮአቸው በተቀመጡበት የቢሮ ስልካቸው አቃጨለ። ደዋይዋ ሴት ነበረች። በኋላም አንድ የማስታወሻ ደብተር በቦነያ ከተማ ተጥሎ እንዳገኘች እና በላዩ ላይ ስልክ ቁጥር አግኝታ መደወሏን በመናገሯ ወንጌላዊው በደስታ ከተቀመጡበት ተነስተው አጨበጨቡ። ደዋይዋንም በከተማው ወዳለ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሄዳ እንድትሰጥላቸው ጠቆሟት እና ከዚያ መቀበል እንደሚችሉ ነገሯት። ጠፍቷል ብለው ተስፋ የቆረጡበትን ትልቅ የአገልግሎት መርጃቸውን እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ መልሶ እጃቸው ላይ አስገባ።


የዚህ ታሪክ ጸሐፊም ይህንን በወንጌላዊ ኬዳሞ እና በቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን መሪዎች ላይ የተቃጣ ጥቃት እና የእግዚአብሔርን አስደናቂ ጥበቃ የሁለተኛው ክፍል የወንጌላዊ ኬዳሞ የአገልግሎት ምዕራፍ መዝጊያ እና የአዲስ የአገልግሎት ምዕራፍ መክፈቻ አመልካች ምልክት እንዲሆን ተረከላችሁ።




ለ22 ዓመታት ያገለገልኩበት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ጸሎት ቤት



ለ22 ዓመታት ያገለገልኩበት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ጸሎት ቤት መድረክ ላይ ቆሜ




ጌጃ በገባሁበት ዓመት በተጀመረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ




ከአንጋፋዎቹ የጌጃ ቃለ ሕይወት መሪዎች እና አገልጋዮች ጋር





በጌጃ ቃለ ሕይወት የወንጌላውያን ቢሮ





ከተማሪዎቼ ጋር





በጌጃ ማገልገል



ከጌጃ ቃለ ሕይወት መሪዎች እና ምዕመናን ጋር




የአስር ሰው አእምሮ የያዘው ሽመልስ ወዳጆ




ተተኪዎቼ ብዬ ከያዝኳቸው በአንዱ
በሚካኤል ሠርግ ላይ ሌሎቹ ሚዜ ሆነው







በአሜሪካ



እኔና መርኪና ከፖል ቢልስኪ ጋር





በአሜሪካ እና ካናዳ ከአቶ መርኪና ጋር




አሜሪካውያንን ማገልገል



ካናዳውያንን ማገልገል











በጌጃ ካፈረኋቸው ልጆቼ ጋር በአሜሪካው የማራ ባህታ ቤት ተሰባሰበን



እስራኤል በገሊላ ባህር ላይ



በጌታ መቃብር አጠገብ


ከጥብርያዶስ ባህር በስተጀርባ ባለ ሆቴል ውስጥ


በእስራኤል




"እንኳን ደህና መጣችሁ" ከታምራት ኃይሌ ጋር ስዊድን ስንደርስ


ጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከሸለመኝ የክብር ዲግሪ ጋር


4 Evangelists
82 Stations
Support



መላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያንን የወንጌል አዝመራ
ገልብጠው ያረሱት አራቱ ብሔራዊ ወንጌላውያን



እኔና ፓ/ር በቀለ ወልደኪዳን
በስዊድን



በስዊድን እኔና ፓ/ር በቀለ ካገለገልናቸው
የእስካንዲኔቪያን አገራት አማኞች ጋር



ድንገት አንድ ላይ ታመው ድንጋጤ
ውስጥ የከተቱኝ ልጄ ሳራ እና
ባለቤቴ ታደለች






እንግዶችን መቀበል የሚሰጠው ደስታ እና የታደለች ጨዋታ ጥርስ አያስከድንም



በቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት
የሠራተኞች የማለዳ ጸሎት ላይ ሳስተምር



ከቃለ ሕይወት መሪዎች እና
አገልጋዮች ጋር



እንደገና ወደ አሜሪካ